

# የምልጃ አገልግሎት ሥልጠና

ከHarverst International Institute ተወስዶ

በአማኑኤል የአምልኮ ማዕከል ኒው ጀርሲ

ተተርጉሞ የቀረበ

2017

## ማውጫ


ክፍል 1 - የጸሎት መጀመሪያ ትምህርት ........ 1

ክፍል 2 - የምልጃ ጸሎት ........ 7

ክፍል 3 - መንፈሳዊ ሃብታችን ለምልጃ ጸሎት ........ 11

ክፍል 4 - እንዴት እንማልድ ........ 19

ክፍል 5 - የምልጃ ጸሎት እንቅፋቶች ........ 25

ክፍል 6 - ጌታ ያስተማረን ጸሎት ለምልጃ ........ 29

ክፍል 7 - ምልጃ ለመንፈሳዊ ተሃድሶ ........ 39

ክፍል 8 - ምልጃን መጀመርና ማቀጣጠል ........ 49

2017 አማኑኤል የአምልኮ ማዕከል በኒው ጀርሲ
ለምልጃ አገልግሎት ሥልጠና ብቻ የተዘጋጀ

በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአብዛኛው የተወሰዱት
ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
ይህንን ጽሑፍ አባዝቶ ለሽያጭ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

# ክፍል 1
# የጸሎት መጀመሪያ ትምህርት

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፡-

- ጸሎት ምን ማለት ነው?
- ጸሎት እንዴት ይመለሳል?
- የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸሎት ሕይወት ምን ይመስል ነበር?
- የጸሎት ደረጃዎች ምንድን ናቸው?
- የጸሎት አይነቶች ስንት ናቸው?

### ቁልፍ ጥቅስ፡-

> ***"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።"*** (ማቴዎስ 7፥7-8)

## ጸሎት ምን ማለት ነው?

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መገባባት ነው። ይህም የተለያየ መልክ አለው፤ መሠረታዊ የሆነው ትርጓሜ ግን ሰው እግዚአብሔርን፣ እግዚአብሔር ደግሞ ሰውን ሲያነጋግረው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ጸሎትን እንዲህ ይገልጠዋል፡-

| | |
|---|---|
| የእግዚአብሔርን ስም መጥራት | ዘፍጥረት 12፥8 |
| ወደ እግዚአብሔር መጮኽ | መዝሙር 27፥7፤ 34፥6 |
| ወደ እግዚአብሔር መቅረብ | መዝሙር 73፥28፤ ዕብራውያን 10፥22 |
| በፊቱ መቆምና እርሱን መጠበቅ | መዝሙር 5፥3 |
| ነፍስን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት | መዝሙር 25፥1 |
| ልብን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት | ሰቆቃው ኤርምያስ 3፥41 |
| ልብን በእግዚአብሔር ፊት ማፍሰስ | መዝሙር 62፥8 |
| ነፍስን በእግዚአብሔር ፊት ማፍሰስ | 1ኛ ሳሙኤል 1፥15 |
| ወደ ሰማይ መጮኽ | 2ኛ ነገሥት 32፥20 |
| እግዚአብሔርን መለመን/መማጸን | ዘጸአት 32፥11 |
| እግዚአብሔርን መፈለግ | ኢዮብ 8፥5 |
| የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ | መዝሙር 27፥8 |
| የእግዚአብሔርን ምሕረት መፈለግ | ኢዮብ 8፥5፤ ኤርምያስ 36፥7 |

ጸሎት ለእግዚአብሔር መናገር ብቻ ሳይሆን፣ እርሱንም መስማት ነው። ጸሎት በእኛ መናገር ላይ ብቻ ከተመሠረተ፣ የጸሎት ሕይወታችን እድሜና ፍሬ አይኖረውም። ስትጸልይ እግዚአብሔር እንዲናገርህ ተጠባበቀው። እርሱ በአብዛኛው ጊዜ በቅዱስ ቃሉ፣ እንዲሁም በልባችን ድምጹን ያሰማናል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በሕልም፣ በራእይ ወይም ደግሞ በልሳን ስንጸልይ ትርጓሜውን በመስጠት ይናገረናል።

በውስጥህ ያለውን ጸሎት ጸልየህ ብቻ አትጨርስ፣ እርሱን ለመስማት ጊዜ ውሰድ። ስንሰማው ለጥያቄያችን መልስ ሆነ ለቀናችን ምሪት ይሰጠናል ወይም ደግሞ በኑሮአችን ልናስቀድመው የሚገባንን ነገር ይሳየናል። አንድአንድ ጊዜ ደግሞ ለምንጸልይላቸው ሰዎች የማበረታቻ፣ የምክር፣ የግሣጼ ወይም የመገለጥ ቃል ይሰጠናል።

ስንጸልይ ሰውነታችን በተለያየ አኳሃን ሆኖ ልንጸልይ እንችላለን። ይህም ማለት፦

| | |
|---|---|
| ቆሞ መጸለይ | 1ኛ ነገሥት 8፥22፤ ማርቆስ 11፥25 |
| ዝቅ ብለን በስግደት መጸለይ | መዝሙር 95፥6 |
| ተንበርክከን መጸለይ | 2ኛ ዜና 6፥13፤ መዝሙር 95፥6፤ ሉቃስ 22፥41፤ የሐዋሪያት ሥራ 20፥36 |
| በግንባራችን ተደፍተን መጸለይ | ዘኍልቁ 16፥22፤ ኢያሱ 5፥14፤ 1ኛ ዜና 21፥16፤ ማቴዎስ 26፥39 |
| እጃችንን ዘርግተን መጸለይ | ኢሳይያስ 1፥15፤ 2ኛ ዜና 6፥13 |
| እጃችንን አንስተን መጸለይ | መዝሙር 28፥2፤ ሰቆቃው ኤርምያስ 2፥19፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥8 |

## ጸሎት እንዴት ይመለሳል?

መጽሐፍ ቅዱስ ጸሎታችን እንዴት እንደሚመለው ሲያስተምር፦

| | |
|---|---|
| በፍጥነት ይመለሳል | ኢሳይያስ 65፥24፤ ዳንኤል 9፥21-23 |
| ዘግይቶ ይመለሳል | ሉቃስ 18፥7 |
| መልሱ እንደፈለግነው አይሆንም | 2ኛ ቆሮንቶስ 12፥8-9 |
| ከምንገምተው በላይ ይሆናል | ኤርምያስ 33፥3፤ ኤፌሶን 3፥20 |

## የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸሎት ሕይወት ምን ይመስል ነበር?

ጸሎት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ከነበረ፣ በእኛ ሕይወት ውስጥ የበለጠ ያስፈልገናል። ጌታችን ኢየሱስ የምልጃ ጸሎት ታላቁ ምሳሌያችን ነው። ስለ ክርስቶስ የጸሎት ሕይወት የሚከተሉትን ጥቅሶች አጥና።

**ጸሎት በክርስቶስ ሕይወት ቀዳሚ ነበር፦**

- በቀንም በሌሊትም ይጸልይ ነበር — ሉቃስ 6፥12-13
- ጸሎትን ከምግቡ ያስቀድም ነበር — ዩሐንስ 4፥31-32

- ጸሎትን ከማንኛውም ተግባር በፊት ያስቀድም ነበር ዩሐንስ 4፥31-32
- ጸሎትን ለደቀመዛምርቱ አስተማራቸው ማቴዎስ 6፥9-13

**ጸሎት በሕይወቱ ከተፈጸሙ ዋነኛ ወቅቶች ጋር የተያያዘ ነበር፦**

| | |
|---|---|
| • ሲጠመቅ | ሉቃስ 3፥21-22 |
| • አገልግሎቱን ሲጀምር | ማርቆስ 1፥35፤ ሉቃስ 5፥16 |
| • ደቀመዛሙርት ከመምረጡ በፊት | ሉቃስ 6፥12-13 |
| • 5ሺህ ሰዎች ከመመገቡ በፊትና በኋላ | ማቴዎስ 14፥19፣ 23፤ ማርቆስ 6፥41፣ 46 |
| • ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ ነህ ሲለው | ሉቃስ 9፥18-20 |
| • በደብረ ዘይት የክብር ተራራ | ሉቃስ 9፥28-29 |
| • ሰብአው በደስታ ሲመለሱ | ማቴዎስ 11፥25፤ ሉቃስ 10፥21 |
| • በአልዓዛር መቃብር ፊት | ዩሐንስ 11፥41-42 |
| • ልጆችን ሲባርክ | ማቴዎስ 19፥13 |
| • ስለ ጴጥሮስ | ሉቃስ 22፥32 |
| • መንፈስ ቅዱስ ስለመምጣቱ | ዩሐንስ 14፥16 |
| • ከኤማሁስ መንገደኞች ጋር | ሉቃስ 24፥30-31 |
| • ከመነጠቁ በፊት | ሉቃስ 24፥50-53 |
| • ለሚያምኑበት ሁሉ | ዩሐንስ 17 |
| • ከመስቀሉ በፊት | ማቴዎስ 26፥26-27፤ ማርቆስ 14፥22-23 |

## የጸሎት ደረጃዎች

ሦስት የጸሎት ደረጃዎች፦ መጠየቅ/መለመን፣ መፈለግ፣ ማንኳኳት

**"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።"** ማቴዎስ 7፥7-8

**መጠየቅ/መለመን የመጀመሪያው የጸሎት ደረጃ ነው።** ይህ የጸሎት ደረጃ ጥያቄያችንን በእግዚአብሔር ፊት አቅርበን መልሳችንን ወዲያው ስንቀበል ነው። ለመቀበል መጠየቅ ነው የሚያስፈልገው፦ **"… አትጠይቁምና አትቀበሉም።"** (ያዕቆብ 4፥2)

**መፈለግ ጠለቅ ያለ የጸሎት ደረጃ ነው።** በዚህ ደረጃ የጸሎት መልስ ልክ እንደመጠየቅ ደረጃ ፈጥኖ አይመጣም። 120 ደቀመዛሙርት በሰገነቱ ላይ ተሰብስበው አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል በጸሎት ሲጠብቁና እግዚአብሔርን ሲፈልጉ እናነባለን። የጸሎታቸው መልስ እስከሚመጣ ድረስ ይጸልዩ ነበር (የሐዋሪያት ሥራ 1 - 2)።

**ማንኳኳት ደግሞ ጥልቅ የጸሎት ደረጃ ነው።** ይህ ደረጃ መልስ ባይመጣም በጽናት የምንጸልየው ጸሎት ነው። ሉቃስ 11÷5-10 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደጠቀሰው ምሳሌ አይነት ነው። በተጨማሪም በዳንኤል ምእራፍ 10 ላይ እንደተጠቀሰውም ማለት ነው።

## የጸሎት ዓይነቶች

ጳውሎስ አማኞችን በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና እንዲጸልዩ ያሳስባል። **"በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ።"** (ኤፌሶን 6÷18) እስኪ የጸሎት ዐይነቶችን እንመልከት፡-

1. **ምስጋናና አምልኮ፡-**

- ወደ እግዚአብሔር ሕልውና የምንገባው በምስጋናና በአምልኮ ነው (መዝሙር 100÷4)።
- አምልኮ ለእግዚአብሔር ያለን አክብሮትና መሰጠት ነው። ምስጋና እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገሮችና ስለማንነቱ የሚገባውን ምስጋና ስናመጣለት ነው።
- እግዚአብሔር የሚመለከው በእውነትና በመንፈስ ነው (ዮሐንስ 4÷23-24)።
- እግዚአብሔርን በእውነት ማምለክ ስንል ራሱን ለእኛ በቃሉ ውስጥ በገለጠው መሠረት ማለት ነው። ስናመልከው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ በፍጹም ልባችን እርሱን ከሁሉ በማስቀደም ነው። በመንፈስ ስናመልክ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን ፈቅደናል ማለት ነው። ይህ ዐይነቱ አምልኮ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚከናወን ነው ማለት ነው።
- ምስጋናንና አምልኮን ስናቀርብ፡-
  - በዝማሬ — መዝሙር 9÷2፣ 11፤ 40÷3፤ ማርቆስ 14÷26
  - ቃል አውጥተን — መዝሙር 103÷1
  - በእልልታ/ጭኸ ብለን — መዝሙር 47÷1
  - እጃችንን በማንሳት — መዝሙር 63÷4፤ 134÷2፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2÷8
  - በማጨብጨብ — መዝሙር 47÷1
  - በሙዚቃ መሣሪያዎች — መዝሙር 150÷3-5
  - ቆመን — 2ኛ ዜና 20÷19
  - እየሰገድን — መዝሙር 95÷6
  - እያሸበሸብን — መዝሙር 149÷3

- እየተንበረከክን መዝሙር 95÷6
- በሆዳችን ተኝተን መዝሙር 149÷5 ፍጽም ለእርሱ መሸነፍና በእርሱ መወረስን የሚያሳይ ነው

**2. መስጠት፦**

- ሕይወታችንንና ፈቃዳችንን ለእርሱ በማስገዛት ስንጸልይ።
- ራስን ለእግዚአብሔር፣ ለሥራውና ለዓላማው በመቀደስና ራሳችንን በመስጠት የምንጸልየው ጸሎት ነው።

**3. አቤቱታን/ልመናችንን ማቅረብ፦**

- አቤቱታ ስንል ጥያቄያችንን ማቅረብ ማለት ነው። የምንጠይቀው ደግሞ በቃሉ ላይ እንደተገለጠው እንደፈቃዱ ስናቀርብ ነው።
- ጥያቄያችንን አለአማራጭ ከልባችን ለእግዚአብሔር ስናቀርብ ነው።
- በሦቱም የጽሎት ደረጃዎች ውስጥ ይህ ዐይነቱን ጸሎት ልንጸልይ እንችላለን - ጠይቅ፣ ፈልግ፣ አንኳኳ።

**4. ንስሃ፦**

- ስለ ኃጢአት ይቅርታ በኑዛዜ እግዚአብሔር እንዲያነፃ መጠየቅ።
- **"በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ** ነው።" 1ኛ ዮሐንስ 1÷9

**5. ምልጃ**

- ይህ ስለ ሌሎች የምንጸልየው ጸሎት ነው። የምልጃ ሰው በሌላው ሰው ጫማ ውስጥ ሆኖ ልክ እንደ ግለሰቡ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ ማለት ነው። ይህንን ነው በዚህ ሥልጠና ውስጥ በስፋት የምንማረው።

# ማስታወሻ

# ክፍል 2
# የምልጃ ጸሎት

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፡-

- የምልጃ ጸሎት ምንድን ነው?
- አማኝ እንደ ምልጃ ሰው መቆም የሚያስችለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ ምንድን ነው?
- የምልጃ ጸሎት ምሳሌያችን ማነው?
- የምልጃ ጸሎት እንዴት ይጸለያል?
- የምልጃ አስፈላጊነት

## ቁልፍ ጥቅስ፡-

**"ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።"** (ዕብራውያን 7፥25፤ አ.መ.ት.)

## የምልጃ ጸሎት ምንድን ነው?

ባለፈው ትምህርታችን ምልጃ ለሌሎች መጸለይ እንደሆነ በአጭሩ ተመልክተን ነበር። የምልጃ ሰው ስንል በሚጸልይለት ሰው ቦታ ሆኖ ወይም የእርሱን ጉዳይ ይዞ ሲቃትት ነው።

**ምልጃ አንዱ ስለ ሌላው ጉዳይ ወይም በአንድ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ በቅድስና፣ በእምነትና በጽናት ሆኖ መጸለይ ነው።**

## አማኝ እንደ ምልጃ ሰው መቆም የሚያስችለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ ምንድን ነው?

- በአዲስ ኪዳን ቀዳሚው የምልጃ አገልጋይ ለመሆን የሚያበቃን መሠረት ጥሪያችን ለክሕነት መሆኑ ነው።
- የእግዚአብሔር ቃል፡-
  - በ1ኛ ጴጥሮስ 2፥5 ላይ ቅዱስ ካህናት፣
  - በ1ኛ ጴጥሮስ 2፥9 ላይ የንጉሥ ካህናት፣
  - በራእይ 1፥6 ላይ ደግሞ አምላኩንና አባቱን እንድናገለግል መንግሥትና ካህናት ላደረገን ይላል።
- የዚህ ጥሪ ጥንታዊ መሠረቱ ደግሞ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን ሲሆን ሌዋውያን የተጠሩበትን የምልጃ አገልግሎት ነው።
- ይህ አገልግሎት ሁለት ኃላፊነት አሉት፡-

1. **በእግዚአብሔር ፊት መቆም** - በመሥዋእትና በመባ እግዚአብሔርን ለማገልገል።
2. **በእግዚአብሔርና በሰው መሐል መቆም** - በጻድቁና እግዚአብሔርና በኃጢአተናው ሰው መካከል በመቆም በደም መስዋዕት ሁለቱን አንድ ጋር ለማምጣት።

- ዕብራውያን 7፥11-19 በብሉይና በአዲስ ኪዳን ያለውን የክህነት አገልግሎት በሚገባ ያብራራል።
  - በብሉይ ኪዳን ክህነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሰጠው ለሌዊ ዘር ብቻ ነበር።
  - በአዲስ ኪዳን ግን እንደ መልከጸዴቅ ክህንት ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ነው። እኛም ክህነትን የተቀበልነው በደሙ ከመንፈስ ተወልደን አዲስ ፍጥረት ስለሆንን ነው።

## የምልጃ ጸሎት ምሳሌያችን ማነው?

- ክርስቶስ የተላከበት ዋነኛው የእግዚአብሔር ዓላማ አማላጃችን እንዲሆን ነው፡-

**"... እግዚአብሔር ተመለከተ፤ ፍትሕ በመታጣቱ ዐዘነ። ማንም እንደሌለ አየ፤ ወደ እርሱ የሚማልድ ባለመኖሩ ተገረመ፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ ድነት አመጣለት፤ የራሱም ጽድቅ ደግፎ ያዘው።"** (ኢሳይያስ 59፥15-16፤ አ.መ.ት.)

- ጌታችን ኢየሱስ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት በአባቱ ፊት፣ እንዲሁም መካከለኛ ሆኖ ይቆማል፡-

**"አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው"** (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5፤ አ.መ.ት.)

**"ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል።"** (ሮሜ 8፥34፤ አ.መ.ት.)

**"ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።"** (ዕብራውያን 7፥25፤ አ.መ.ት.)

- ጌታችን ኢየሱስ በጻድቁ እግዚአብሔርና በኃጢአተኛው ሰው መካከል ጣልቃ ገብቶ የገዛ ደሙን መስዋዕት አድርጎ አቀረበና ዕርቅን አመጣ።
- ከክርስቶስ ደም የተነሣ ነው ዛሬ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት መቅረብ የሚቻለው (ዕብራውያን 4፥14-16)።
- ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ይማልድ ነበር። ይህም ለበሽተኞች ሲጸልይ፣ አጋንንትን ሲያስወጣ፣ ለደቀመዛሙርቱ ሲጸልይ፣ ወዘተ. ... ይታይ ነበር። ይህንንም ተግባሩን ካረገም በኋላ በአባቱ ቀኝ ሆኖ ቀጥሏል።

## የምልጃ ጸሎት እንዴት ይጸለያል?

- በብሉይም በአዲስም የምልጃን አገልግሎት ስንመለከት እንደቆየነው ሁሉ ምልጃ በእግዚአብሔር ፊት መቆም፣ እንዲሁም በጻድቁ እግዚአብሔርና በሰው መካከል መቆም ነው። በመካከል መቆማችንን ፍሬያማ የሚያደርገው አስቀድመን በእግዚአብሔር ፊት በመቆም የምናሳድገው ጥልቅ ወዳጅነት ነው።
- ዘኅልቁ ምእራፍ 14 በመጽሐፍ ቅዱሳችን የምናገኘው የምልጃ ጸሎት ትልቅ ምሳሌ ነው። በተደጋጋሚ የሙሴን ሕይወት ስንመለከት ለሕዝቡ ከመማለዱ በፊት በእግዚአብሔር ሕልውናና ክብር ውስጥ ሲቆም እናነባለን። በዘኁልቁ 14 ላይ ግን ስናነብ፣ ለምልጃ ጸሎት ዓይነተኛ ምሳሌ እናነባለን። (ይነበብ)
- በዘኁልቁ 12÷7-8 ላይ እንዲህ ይላል፡- **"ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፥ በምሳሌ አይደለም፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፤ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራችሁም? አለ።"**
- የአዲስ ኪዳን አማኞች እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን የእንስሳትን መስዋዕት በእግዚአብሔር ፊት አያቀርቡም። የሚያቀርቡት መስዋዕት ቢኖር የከንፈሮችን ፍሬ (ዕብራውያን 13÷5)፣ እንዲሁም ሰውነታቸውን ህያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርገው ነው (ሮሜ 12÷1-2)።
    - ይህ ደግሞ የሚያመለክተ ከጌታ ጋር ስላለው ጥልቅ ሕብረትና ወዳጅነት (Intimacy) ነው።
    - ከዚህ የተነሣ በፊቱና ስለሌሎች በመካከል በመቆም የምልጃን ጸሎት እንድናከናውን የበቃን ያደርገናል።
- ሐዋሪያው ጴጥሮስ ይህንን የተቀበልነውን የክኅነት አገልግሎት በሁለት ቃላት ይገልጠዋል፡- "ቅዱስ" እና "የንጉሥ" (1ኛ ጴጥሮስ 2÷9)።
    - ቅድስና፡- በእግዚአብሔር ፊት ስለምንቆም። ያለ ቅዱስና እግዚአብሔርን ማየት አይቻልምና (ዕብራውያን 12÷14)። ይህም ጽድቅ በእኛ ላይ ሳይሆን በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ነው።
    - የንጉሥ፡- ሲል ደግሞ የመንግሥትን ሥልጣን የሚያመለክት ሲሆን ይህንንም ያገኘነው የንጉሥ ቤተሰብ ስለሆንን ነው (Royal Family)። ይህም ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት ከክርስቶስ ደም የተነሣ መግባት ስለቻልን ማለት ነው።
- ምልጃ አንዳንድ ጊዜ ካገኘነው መረጃ ሊጀምር ይችላል። ይህም ከሰውና ከሁኔታዎች ከተገነዘብነው ተነስተን የምንጸልየው ነው። (ምሳሌ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2÷1-2)
- አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምልጃ የምንካሄደው በመንፈስ ቅዱስ ይሆናል። ይህም በመንፈሳችን ውስጥ ከተቀመጠው ሸክም የተንሣ ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ በእኛ ውስጥ ሆኖ ይቃትታል። በዚህ ጊዜ የምንጸልየው በመንፈሳዊ ልሳን ይሆናል ማለት ነው።
    - ሮሜ 8÷26 – **"እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል"**
    - 1ኛ ቆሮንቶስ 14÷2 – **"በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል"**

- በልሳን በምንጸልይበት ጊዜ በአእምሮአችን ስለ ምን እንደምንጸልይ አናውቅም። ይህ ዓይነቱ ምልጃ ጠለቅ ያለና መሥራቱ የማያጠራጥር ነው፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የሚጸልየው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነውና። በልሳን ስንጸልይ አእምሮአችንና ፈቃዳችን መንፈስ ቅዱስ በሚጸልየው ጸሎት ውስጥ ጣልቃ ሊገቡ አይችሉም።

## የምልጃ ጸሎት ለምን ያስፈልጋል?

- የክርስቶስን ፈለግ መከተል ስላለብን።
- የእምነት አባቶችና እናቶች የሄዱበትና ታላላቅ ፍሬ ያፈሩበት አገልግሎት ስለሆነ።
- ምልጃ ዓለምን ሁሉ በመንፈስ እንድንቃኝ የሚያስችለን አገልግሎት ስለሆነ። *(ለሶሪያው ንጉሥ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ)* **"ባሪያዎቹም አንዱ፦ ጌታዬ ሆይ፥ እንዲህ አኮ አይደለም፤ ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል አለ።"** (2ኛ ነገሥት 6፥12)
- የምልጃ ጸሎት ርቀትን፣ ባሕልን፣ ጂኦግራፊን፣ መንግሥታትን፣ ተቋማትን ጥሶ የመግባት ኃይል አለው።
- በግለሰቦችና በመንግሥታት ሩጫ መሐል በእግዚአብሔር ፈቃድ ጣልቃ የምንገባበት አገልግሎት ነው።
- ለሰዎች ድኅነት እጅግ አስፈላጊ የሆነ አግልግሎት ነው።

<u>ማስታወሻ</u>

# ክፍል 3
# መንፈሳዊ ሃብታችን ለምልጃ ጸሎት

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፡-

- ኃይልና ሥልጣን
- ማሰርና መፍታት
- የኢየሱስ ስም
- የኢየሱስ ደም
- ጾም
- እንዴት እንደምንጠቀምባቸው

## ቁልፍ ጥቅስ፡-

> **"ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት በአንድነት ጠርቶ አጋንንትን ሁሉ እንዲያወጡ፣ ደዌንም እንዲፈውሱ ኀይልና ሥልጣን ሰጣቸው"** (ሉቃስ 9፥1፤ አ.መ.ት.)

## መግቢያ

ለተጠራንለት የምልጃ አገልግሎት እግዚአብሔር ከፍ ያሉ መንፈሳዊ ሃብቶች (Spiritual resources) አዘጋጅቶልናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ እነዚህ ሃብቶቻችን ምን እንደሆኑን እንዴት እንደሚሠሩ እንማራለን።

## ኃይልና ሥልጣን

- በምልጃ ጸሎት ውስጥ ከጠላታችን ሰይጣን ጋር ስለወንዶች፣ ስለሴቶች፣ ስለልጆች፣ ስለሃገራት፣ ስለመንፈሳዊና ስለ መንግሥታት መሪዎች ውጊያ እንገጥማለን።
- ይህንንም ውጊያ የምናካሄደው በገዛ አቅማችን ሳይሆን በመንፈሳዊ ሃብቶቻችን ታጅበን ነው።
- **"ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት በአንድነት ጠርቶ አጋንንትን ሁሉ እንዲያወጡ፣ ደዌንም እንዲፈውሱ ኀይልና ሥልጣን ሰጣቸው"** (ሉቃስ 9፥1፤ አ.መ.ት.)
- በሥልጣንና በኃይል መካከል ልዩነት አለ። ለምሳሌ አንድን ፖሊስ እንደምሳሌ እንውሰድ፡-
    - የፖሊስ አርማ ያለበት መለዮ ይለብሳል።
    - የማዕረጉ ምልክቶች በመለዮው ላይ ተደርገዋል።
    - ያለው ሥልጣን ደግሞ በሚያገለግለው መንግሥት የተሰጠው ደረጃ ነው።

- ሁሉም ደግሞ ማንነቱን አውቆ ባያከብረው ደግሞ ራሱን ለመከላከልና ሕግን ለማስጠበቅ በመንግሥት መሣሪያ እንዲታጠቅ ይደረጋል።
- ልክ እንደዚሁ በጠላት ላይ የተሰጠን ሥልጣን በክርስቶስ ሲሆን ይህም በእርሱ ከማመናችን የተነሣ ነው።
- ጠላትን የምንዋጋበት ኃይል ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የምናገኘው ነው። **"እኔም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ።"** ሉቃስ 24፥49
- ልክ እንደ ፖሊሱ ፥ እኛም ለተዋጣለት የምልጃ አገልግሎት ሥልጣንም ኃይልም ያስፈልገናል። ምክንያቱም በእርግጥም ውጊያችን በሰማያዊ ሥፍራ ከጠላት ጋር ነውና።
- ሥልጣንን ያገኘነው በዳግም ልደት ሲሆን፣ ኃይል የምንቀበለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነው። ስለዚህ ነው በድኅነት ላይ ማቆም የሌለብን፤ ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅና ኃይልን ለመቀበል መራብ ያለብን።
- ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የምልጃን አገልግሎት በሙላት እንድናገለግል ሥልጣንና ኃይል በአንድነት በእኛ ሊሠሩ ይገባል።
- ሰይጣን ፍጡር እንደመሆኑ ውሱን ኃይል ነው ያለው፤ ነገር ግን ሥልጣን የለውም። ለእኛ ግን ሥልጣንም ኃይልም በጠላት ሁሉ ላይ ተሰጥቶናል።
- ጌታ ኢየሱስ የሰጠን ኃይል በጠላትና በሥራው ላይ ብቻ እንጂ በሰው ላይ እንድንጠቀምበት አይደለም።

## ኃይል በጠላት ላይ፦

ነጻ መውጣት ሆነ ፈውስ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የመማለድ ሥልጣንና ኃይል አለን፦

- ***"ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት በአንድነት ጠርቶ አጋንንትን ሁሉ እንዲያወጡ፣ ደዌንም እንዲፈውሱ ኀይልና ሥልጣን ሰጣቸው"*** (ሉቃስ 9፥1፤ አ.መ.ት.)

## ኃይል በኃጢአት ላይ፦

ሰዎች እንዲድን የምልጃ ጸሎት ማካሄድ እንችላለን፦

- **"የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ብትሉ፣ ኀጢአታቸው ይቅር ይባልላቸዋል፤ ኀጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ግን፣ ይቅር አይባልላቸውም።"** ዩሐንስ 20፥23

## ኃይል ስለወንጌሉ መስፋፋት፦

የመንግሥት ሠራተኞችን ጌታ እንዲልክ ለመማለድ ሥልጣን ተሰጥቶናል፦

- ***"ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤ 'መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።'"*** (ማቴዎስ 9፥37-38)

## ማሰርና መፍታት

- ማሰር የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ስንመለከተው **"አሳር"** የሚለው ቃል ሲሆን (አማርኛው ቃል ተቀራራቢ ነው)። አሠረ ሲል ትርጉሙ፡-
  - ወደረ ወይም ጠረዘ (bind)
  - በእስር ቤት ጣለ (imprison)
  - ቋጠረ (tie)
  - ከበበ - ከበባ (gird)
  - ገደበ፣ ጫና አደረገ (harness)
- ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ወደ 70 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን በአብዛኛው የሚያመለክተው ፈረሶችንና አህዮችን ከማሰር ጋር ነው።
  - **"ስለዚህ ሄደው የከተማዪቱን መግቢያ በር ጠባቂዎች ጮኸው በመጥራት፣ "ወደ ሶርያውያን ሰፈር ገባን፤ እዚያም ከታሰሩ ፈረሶችና አህዮች በቀር አንድም ሰው አልነበረም፤ የማንም ድምፅ አልተሰማም፤ ድንኳኖቹም እንዳሉ ናቸው" ብለው ነገሯአቸው።"** (2ኛ ነገሥት 7፥10)
- ጌታችን ኢየሱስ በዚህ ረገድ በማቴዎስ 12፥28-29 እጅግ አስፈላጊ ነገር ተናግሮአል፡-
  - **"እኔ ግን አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች። ወይስ አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣ አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር እንዴት አድርጎ ይሳካለታል? ኋላም ቤቱን መበዝበዝ ይችላል።"** (ማቴዎስ 12፥28-29)
- ኃይለኛውን ሳያስር ማንም የኃይለኛውን ንብረት ሊነጥቅ አይችልም። ኃይለኛ ተብሎ የተጠራው ሰይጣን ነው።
- ሰይጣን እጅግ ውድ ንብረቴ የሚለው ምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ በጨለማና በባርነት ያሉና በአጋንንት የተያዙ ሰዎች ናቸው።
- ጌታችን ኢየሱስ ለአማኞች የማሰርና የመፍታት ኃይል ሰጥቶአቸዋል፡-
  - **"የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።"** (ማቴዎስ 16፥19)
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክፉ መናፍስት ስለማስወጣት ሲያስተምር የሰጠው መመሪያ፡-
  - አስቀድሞ ኃይለኛውን ማሰር
  - አጋንንትን ማስወጣት
- በሕይወታችን፣ በቤታችን፣ በአካባቢያችንና በቤተክርስቲያናችን የሚሠራውን ጠላት በማሰር የተላከንበትን ሥራ መስራት እንችላለን። **ስለዚህ ለመሥራት <u>ማሰር</u> ወሳኝ ነው!**
- ጠላትን ካሰርን በኋላ ደግሞ ፥ ሰዎችን ጠላት ከሚሠራባቸው የኃጢአት እስራት፣ የሚጫጫን መንፈስ፣ ተስፋ ማስቆረጥ ልንፈታቸው እንችላለን።

- ለእያንዳንዱ ሁኔታ፣ ችግርና ተግዳሮት መንፈሳዊ ቁልፍ አለ። ይህም ቁልፍ ያለው በማሰርና በመፍታት በሚደረገው የምልጃ ጸሎት ውስጥ ነው።

## የኢየሱስ ስም

የኢየሱስ ስም የምንማልድበት ሥልጣናችን ነው። ጌታችን እነዚህን የሚከተሉትን የተስፋ ቃሎች ሰጥቶናል፡-

- ***"ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ፣ እኔ አደርገዋለሁ።"*** (ዮሐንስ 14፥14)
- ***"በዚያ ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም፤ እውነት እላችኋለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።"*** (ዮሐንስ 16፥23)
- ***"የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤ እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤ የሚገድል መርዝ ቢጠጡ እንኳ አይጐዳቸውም፤ እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ።"*** (ማርቆስ 16፥17-18)
- ***"ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ 'ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።'"*** (ማቴዎስ 28፥18-19)

ለመጸለይ፣ ለመስበክ ለማስተማር፣ ለማጥመቅ፣ አጋንንትን ለማስወጣት፣ ለመፈወስና የጠላትን ሥራ ሁሉ ለማፍረስ የኢየሱስ ስም ተሰጥቶናል። ስሙ ከስሞች ሁሉ በላይ ነው።

- ***"የተቀመጠውም ከግዛትና ከሥልጣን፣ ከኀይልና ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው።"*** (ኤፌሶን 1፥21)
- ***"ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጕልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።"*** (ኤፌሶን 2፥9-11)

## የኢየሱስ ደም

ሌላው ለምልጃ ትልቁ መንፈሳዊ ኃብታችን የኢየሱስ ደም ነው። ወደ አብ የምንገባው በእርሱ ደም ነውና።

- ***"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ በኢየሱስ ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ድፍረት አግኝተናል፤ ይኸውም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል በከፈተልን አዲስና ሕያው መንገድ ነው። በእግዚአብሔር ቤት ላይ የተሾመ ታላቅ ሊቀ ካህናት ስላለን ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንንም በንጹሕ ውሃ ታጥበን፣ በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ። የተስፋን ቃል የሰጠን ታማኝ ስለ ሆነ፣ እምነን የምንናገርለትን ተስፋ አጥብቀን እንያዝ።"*** (ዕብራውያን 10፥19-23)

- በመጽሐፍ ቅዱስ ቅድስተ ቅዱሳን እግዚአብሔር ያለበት ቦታ ነው። የእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ ምንም ዓይነት ኃይማኖታዎ ሥርዓት ብንፈጽም እንኳ ልንቆም አንችልም፤ ይህ የሚሆነው በክርስቶስ ደም ብቻ ነው።
- የደም ጉዳይ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራእይ ድረስ እንደ ገመድ ተዘርግቶ እናገኘዋለን።
- ዘሌዋውያን 17÷11፣ 14 – **"የፍጡር ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና … የማንኛውም ፍጡር ሕይወት ደሙ ነውና።"**
- እንግዲህ በሮሜ 6÷23 ላይ የተጻፈው፦ **"የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና"** የሚል ነው። ሕይወት ደግሞ ያለው በደም ውስጥ ነው፤ ከዚህ የተነሣ የኃጢአት ይቅርታ መሠረቱ በደም ስርየት ላይ እንዲሆን እግዚአብሔር ደነገገ።
    - **"በርግጥ ከጥቂት ነገሮች በስተቀር ሁሉም ነገር በደም መንጻት እንዳለበት ሕጉ ያዛል፤ ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና።"** (ዕብራውያን 9÷22)
- የመጀመሪያውን የደም ስርየት የምናገኘው አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሰሩ ጊዜ ሲሆን፣ እግዚአብሔር እንስሳን ገድሎ ቁርበትን አለበሳቸው። ይህም በክርስቶስን የሚገኘውን ጽድቅ የሚያመለክት ጥላ ነበር።
- የደም መስዋዕት በአቤልና ቃየን ታሪክ፣ እንዲሁም በኪዳን ምልክት በሆነው ግዝረት አስፈላጊነቱን እናያለን። በብሉይ ኪዳንም የእንስሳት ደም ለኃጢአት ስርየት በየጊዜው ሲፈስ እናነባለን። የዕብራውያን መጽሐፍ ምእራፍ 8 አሮጌውን ኪዳን ከደም ጋር ያለውን ትስስር ይተነትናል።
- በአዲስ ኪዳን ግን ለሰው ልጆች ኃጢአት እንዲፈስ እግዚአብሔር የወደደው የልጁን ደም ነበር። (ማርቆስ 14÷24) የፍየሎችና የኮርማዎች ደም ከእንግዲህ አያስፈልግም (ዕብራውያን 9÷12)።
- ***"የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ፣ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደሚናገረው ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል።"*** (ዕብራውያን 12÷24)

## ጾም

> ***የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጾሙ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎችም መጥተው ኢየሱስን፣ "የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት ሲጾሙ፣ የአንተ ደቀ መዛሙርት የማይጾሙት ለምንድን ነው?" አሉት። ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤ "ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሊጾሙ አይችሉም፤ ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወቅት ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ግን ይጾማሉ።"***
>
> ማርቆስ 2÷18-19

ለምልጃ ጸሎት ሌላኛው ትልቁ ሃብታችን ጾም ነው። ጾም ማለት ራሱን የሚገልጥ ቃል ሲሆን ምግብ አለመብላት ማለት ነው። የአገልጋይ ሕይወት መገለጫዎች መካከል አንዱ ጾም ነው።

- *"አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ፣ ለማንም ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም። ይሁን እንጂ በምናደርገው ነገር ሁሉ ራሳችንን እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች እናቀርባለን፦ በብዙ ትዕግሥት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በመታሰር፣ በሁከት፣ በሥራ ብዛት፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመራብ፣ በንጽሕና፣ በዕውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር፣ በእውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኀይል፣ በቀኝና በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመያዝ፣ በክብርና በውርደት፣ በመመስገንና በመሰደብ፣ ኖረናል፤ ደግሞም እውነተኞች ስንሆን*

**ሐሰተኞች ተብለናል፤ የታወቅን ስንሆን እንዳልታወቅን ሆነናል፤ ሞተዋል ስንባል እነሆ በሕይወት አለን፤ ብንደበደብም አልተገደልንም፤ ሐዘንተኞች ስንሆን ሁል ጊዜ ደስተኞች ነን፤ ድኾች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን፤ ምንም የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።"** (2ኛ ቆሮንቶስ 6፥3-10)

- በሐዋሪያት ዘመን ቤተክርስቲያን በጾም የተጋች ነበረች።

## የጾም ዓይነቶች

- ሁለት የጾም ዓይነቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን።
    1. <u>ሙሉ ጾም</u> - አለምንም ምግብ። **"ሙሴ እህል ሳይበላ ውሃም ሳይጠጣ ከእግዚአብሔር *(ያህዌ)* ጋር አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በዚያ ነበር፤ በጽላቶቹ ላይ የቃል ኪዳኑን ቃሎች፣ ዐሥርቱ ትእዛዛትን ጻፈ።"** (ዘፀዓት 34፥28)
    2. <u>ከፊል ጾም</u> - የተወሰነ ነገር በመመገብ። "በዚያን ጊዜ እኔ ዳንኤል ለሦስት ሳምንት አለቀስሁ፤ 3ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላሁም፤ ሥጋም ሆነ የወይን ጠጅ ወደ አፌ አልገባም፤ ቅባትም አልተቀባሁም።" (ዳንኤል 10፥3)

## የጾም ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ፦

- የአብርሃም ሎሌ ለይስሃቅ ሚስት ሊፈልግ ሲሄድ ጾሞ ጸልዮ ነበር። (ዘፍጥረት 24፥33)
- ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ሕጉንና የመገናኛውን ድንኳን ንድፍ ሲቀበል 40 ቀንና ሌሊት በመጾም ነበር። (ዘጸዓት 34)
- ሐና ለመውለድ ጾመች (1ኛ ሳሙኤል 1፥7-8)።
- ነህምያ ለእየሩሳሌም መታደስ ጾመ (ነህምያ 1፥4)።
- ሃማ እስራኤል በሙሉ ከምድር እንዲወገድ ያጸደቀውን አዋጅ ለማስገልበጥ ድፍን እስራኤል ጾመ (አስቴር 4)።
- በዮናስ የመጣውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው የነነዌ ከተማ ሕዝብ ጾሙ (ዮናስ 3፥5-10)።
- ዳዊት ከሳዖል ሞት በኋላ ከመንገሡ በፊት ከተከታዮቹ ጋር ጾመ (1ኛ ሳሙኤል 31)።
- ዳንኤል ስለ 70ው ባርነት ዘመን ፍጻሜ 21 ቀን ጾመ (ዳንኤል 9)።
- ንጉሡ ኢዮሳፍጥ ከመጣባቸው ከባድ ውጊያ በፊት ጾም አወጀ (2ኛ ዜና 20፥3)።
- ዕዝራ ከምርኮ ለሚመለሰው ሕዝብ ጉዞ መሳካት ጾም አወጀ (ዕዝራ 8-9)።
- ኢየሱስ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት 40 ቀንና ሌሊት ጾመ (ማቴዎስ 4)።
- ጳውሎስ ሕይወቱን ለክርስቶስ ከሰጠ በኋላ ጾምና ጸሎት የሕይወቱ ዋነኛ ክፍል ነበር።
- ጴጥሮስ ሲጾምና ሲጸልይ ነበር ታላቁን የመጀመሪያውን ተልዕኮ ለአሕዛብ የተቀበለው (የሐዋሪያት ሥራ 10)።
- በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ነብያትና መምህራን እየጸለዩ ሳሉ ነበር፣ ጳውሎስና ሲላስን ለሐዋሪያዊ ጉዞ እንዲለዩአቸው መንፈስ ቅዱስ የተናገራቸው (የሐዋሪያት ሥራ 13፥2)።

## የጾም ዓላማ

- ጾማችን እግዚአብሔርን አይቀይረውም፤ እኛን ግን ይቀይረናል።
- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚመላለስበት መንፈሳዊ ደረጃ ፥ እኛ ከእርሱ ጋር እንዲኖረን እስከፈቀድነው የቅርበት መጠን ነው።
- ለውጥ በእኛ ሕይወት በተከሰተ ቁጥር፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በሚያደርገው ሕብረት ጠቀሜታ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላል።
- የምንጾመው እግዚአብሔርን ሳይሆን ራሳችንን ለመቀየር ነው። ምሳሌ:-
  - ዮናስና የነነዌ ሕዝብ (ትንቢተ ዮናስ)
  - ደቀ መዛሙርትና አልወጣ ያለው ኢጋንንት (ማርቆስ 9፥29)
- በጾም ጸሎት ካልሆነ ውጤት የማናገኝባቸው ጸሎቶች በክርስትና ሕይወትን መንገዳችን ሁልጊዜ ይመጣሉ።
- ጾም ከንቱ የረሃብ አድማ ሳይሆን ዓላማ ያለው ልምምድ ነው። የጾምን አላማ ሳይረዱ መጾም ፍሬ አልባ ያደርገናል። የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለምን ሰዎች እንደጾሙ እናጥና።
  - ዩናስ 3፥5 – ለመጣው ለእግዚአብሔር መልእክት ምላሽ ሲሰጡ
  - ሉቃስ 4፥1 – በምድረበዳ ሲፈተን
  - 2ኛ ዜና 20፥3 – የጦርነት ተግዳሮት እስራኤል ሲገጥማት
  - ዳንኤል 9፥3-4 – የእግዚአብሔርን ምሪት ነብዮ ዳንኤል ሲሻ
  - የሐዋሪያት ሥራ 13፥2-3 – ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን ሲፈልጉ
  - አስቴር 4፥16 – በባለሥልጣናት ፊት እግዚአብሔር ሞገስን እንዲሰጥ ተፈልጐ በነበረበት ጊዜ
  - ማርቆስ 9፥29 - ጠላትን ፊት ለፊት ከመጋጠም በፊት
  - መዝሙር 35፥13፤ 69፥10 – ራስን ለማዋረድ፣ ትህትናን ለመልበስ
  - ኢዮኤል 2፥12 - በንስሃ በእግዚአብሔር ፊት ለመውደቅ
  - ኢሳይያስ 58፥7 - በመንፈስም ሆነ በኑሮ ድሆች የሆኑትን ለመመገብ
  - ኢሳይያስ 58፥6 - የጭቈናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቈኑትን ነጻ እንድታወጡ፣ ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ

## ምን ያህል ጊዜ እንጹም?

- በዚህ ነገር እግዚአብሔርን ማዳመጥ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱን አጭር ወይም ረጅም ጊዜ መጾም እንደሚገባን ይመራናል።
- መጾም ልንለማመደው የምንችለው ነገር ነው። ረጅም ጾም በምንጾምበት ጊዜ ግን ውሃ መጠጣት አስፈላጊ ነው።

## የግልና የሕብረት ጾም

- ጾም በአማኙና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ጉዳይ ነው። ጾማችንን በግል ከአምላካችን ጋር እንጂ በሰዎች ፊት የምንመካበት ነገር አይደለም።

**“ስትጾሙ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ እነርሱ መጾማቸው እንዲታወቅላቸው ሆን ብለው በፊታቸው ላይ የሐዘን ምልክት ያሳያሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል። አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊትህን ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ በዚህም መጾምህ በስውር ያለው አባትህ ብቻ የሚያውቀው፣ ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል።”** (ማቴዎስ 6፥16-18)

- አንዳንድ ጊዜ በቤተክርስትያን ወይም በቅዱስና ሕብረት ሁሉንም የሚጠቀልል ጾም ይታወጃል።
  **“በጽዮን መለከትን ንፉ፤ ቅዱስ ጾምን ዐውጁ፤ የተቀደሰን ጉባኤ ጥሩ።”** (ኢዮኤል 2፥15)

## እግዚአብሔር የመረጠው ጾም (ኢሳይያስ 58)

- ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት የምናዋርድበት ቦታ
- የከፉውን እስራት የምንፈታበት ቦታ
- ታላላቅ ሸክሞች የሚራገፉበት ቦታ
- የተጨቆኑ ነጻ የሚወጡበት ቦታ
- እኔነት ሥፍራ ለቆ ለሌሎች በበጎነትን እንድናደርግ የሚያስችለን ቦታ ነው።

## የጾም ውጤቶች

- በጾምና በጸሎት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጥልናል። **“የዚያን ጊዜ ትጣራለህ፤ እግዚአብሔርም ይመልስልሃል፤ ለርዳታ ትጮኻለህ፤ እርሱም፣ ‘እለሁልህ’ ይልሃል።”** (ኢሳይያስ 58፥9)
- ብርሃንን በጨለማ ያበራል (ኢሳይያስ 58፥8፣ 10) - ሰማያዊ ተጽዕኖ ታመጣለህ
- ኢሳይያስ 58፥11
  - እግዚአብሔር ይመራሃል
  - ፍላጐትህን ያሚላል
  - አጥንትህን ያበረታል
- **“ወገኖችህ የቀድሞ ፍርስራሾችን መልሰው ይሠራሉ፤ የጥንቱንም መሠረት ያቆማሉ፤ አንተም፣ የተናዱ ቅጥሮችን አዳሽ፣ ባለ አውራ መንገድ ከተሞችን ጠጋኝ ትባላለህ።”** (58፥12)
  - የፈረሰው ተመልሶ ይሠራል
  - የጥንቱ መሠረት ተመልሶ ይቆማል
  - ቅጥር አዳሽ ትባላለህ
  - ጠጋኝ ትባላለህ

# ክፍል 4
# እንዴት እንማልድ?

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፡-

- እንዴት እንማልድ
- ለፍሬያማ ምልጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች
- ስለምን እንማልድ
- ተስፋዎች ለምልጃ

## ቁልፍ ጥቅስ፡-

> **"በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል፤ የምንለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን፣ የለመነውንም ነገር እንደ ተቀበልን እናውቃለን።"** (1ኛ ዮሐንስ 5፥14-15፤ አ.መ.ት.)

## መግቢያ

የምልጃ ጸሎት ፍሬያማነቱ ድምጻችንን ከፍ አድርገን ሆነ ወይም በኃይል ከመጸለያችን የተነሳ ሳይሆን ከልብ ከመጸለያችን የሚመነጭ ነው። (ይህንን ስንል ድምጻችንን ከፍ ማድረግም ሆነ በኃይል መጸለያችን ስኅተት ነው ማለት አይደለም) የሰይጣን ዋናው ተልዕኮ እግዚአብሔር እንዳይከብር መትጋት እንደሆነ ሁሉ፣ የምልጃ ጸሎት ደግሞ በተቃራኒ ዋነኛ ውጤቱ እግዚአብሔርን ከብሮ ማየት ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን መክበር ቀዳሚ ዓላማ በማድረግ ሁለንተናችንን ለምልጃ አገልግሎት ስንሰጥ ፥ እግዚአብሔር ራሱ ይገለጣል። **"እናንተም ትጠሩኛላችሁ፤ ቀርባችሁ ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁም ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ፤ እኔም አገኛለችኋለሁ" ይላል እግዚአብሔር፤"** (ኤርምያስ 29፥12-13)

ጸሎታችን በእምነትና በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል፡-

> **"በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል፤ የምንለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን፣ የለመነውንም ነገር እንደ ተቀበልን እናውቃለን።"** (1ኛ ዮሐንስ 5፥14-15፤ አ.መ.ት.)

በዚህ ትምህርት እንዴት መማለድና ስለምን መማለድ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን እንማራለን። በተጨማሪም እንዴት በተስፋ ቃሎች ላይ ጸሎታችን ሊመሠረት እንደሚገባው እንማራለን።

# እንዴት እንማልድ?

- ጸሎት የሚቀርበው ለእግዚአብሔር ነው — መዝሙር 5÷2
- ጸሎት ከንቱ ቃላትን ስለደጋገምን አይደለም የሚሰማልን ወይም የምንደመጠው ከብዛቱ የተነሣ ሳይሆን ከጥራቱ የተነሣ ነው — ማቴዎስ 6÷7
- ከንቱ ቃላት እንደጋግም እንጂ ጸንተን መጸለይ አልተከለከለም — ሉቃስ 11÷5-13፣ 18÷1-8
- በምንረዳው ቋንቋ እንጸልይ (በሁሉ ዓይነት ጸሎት ይላልና) — ኤፌሶን 6÷18
- በልሳን እንማልድ — ሮሜ 8÷26፤ ይሁዳ 20
- እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንማልድ — 1 ዩሐንስ 5÷14-15
- በስውር እንጸልይ — ማቴዎስ 6÷6
- ዘወትር እንጸልይ — ሉቃስ 21÷36
- ሳናቋርጥ እንጸልይ — ሮሜ 12÷12፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5÷17
- በጌታ በኢየሱስ ስም አብን እንጠይቅ — ዩሐንስ 14÷13-14
- ነቅተን እንጸልይ (እንደ ንቁ ጉበኛ) — 1ኛ ጴጥሮስ 4÷7
- የጌታን ትምህርተ-ጸሎት ምሳሌነት ተከትለን እንጸልይ — ማቴዎስ 6÷9-13
- በይቅርታና በምሕረት ልብ ሆነን እንጸልይ (ለጸሎት ስትቆሙ) — ማርቆስ 11÷25
- በትህትና እንጸልይ — ያዕቆብ 4÷1-10
- አንዳንድ ጊዜ ጸሎትን በጾም በጾም አጅበን እንማልድ — ማቴዎስ 17÷21
- ተግተን እንጸልይ — ያዕቆብ 5÷16፤ ቆላስይስ 4÷12
- ለእግዚአብሔር በመገዛት መንፈስ እንጸልይ — ሉቃስ 22÷42
- በመፍታትና በማሰር እንጸልይ — ማቴዎስ 16÷19

## ለፍሬያማ ምልጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች

ከዚህ ቀጥሎ ለፍሬያማ ምልጃ የሚያበቁንን የተወሰኑ ጥቅሶች እናጠናለን፦

1. አስቀድመን በምልጃ አገልግሎት ከኢየሱስ ጋር በክህነት ቢሮ እንድንተባበር የወደደውንና የፈቀደውን እግዚአብሔርን እናመስግነው። (ዕብራውያን 7÷25፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2÷9)
2. በንጹህ ልብ በፊቱ እንቅረብ። ያልተናዘዝነውን ኃጢአት ይዘን ወደ ምልጃ መሔድ የለብንም።
    - **"ኀጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን ኖሮ፣ ጌታ ባልሰማኝ ነበር።"** መዝሙር 66÷18

- ***"እግዚአብሔር ሆይ፤ መርምረኝ፤ ልቤንም ዕወቅ፤ ፈትነኝ፤ ሐሳቤንም ዕወቅ፤ የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ፤ በዘላለምም መንገድ ምራኝ።"*** መዝሙር 139÷23-24

3. ካለመንፈስ ቅዱስ መጸለይ አለመቻላችንን አውቀን ለእርሱ እውቅና መስጠት። (ሮሜ 8÷26) መንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠረን እግዚአብሔርን ልንጠይቅ፣ ይህንንም ልናምንና ስለዚህም ልናመሰግነው ይገባል። (ኤፌሶን 5÷18)
4. በምልጃችን ወቅት ጠላትን ፊት ለፊት እንጋፈጠው። ኃይልን በተላበሰው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና የመንፈስ ሰይፍ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመን ልናጠቃው ይገባል። ***"እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል።"*** (ያዕቆብ 4÷7)
5. በምልጃ ጸሎት ጊዜ ለገዛ ስሜታችንና ምኞታችን እንሙት። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ምልጃችን በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቻችን ላይ የተመሠረተ መረጃ ብቻ እንዳይሆን (ነፍሳዊ ጸሎት) በቃሉና በመንፈሱ ሊመረመር ይገባል።
    - ምሳሌ 3÷5-6 – **"በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል።"**
    - ኢሳይያስ 55÷8 – **"ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ፣ መንገዴ እንደ መንገዳችሁ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር።"**
    - ከነፍሳዊ ጸሎት ወደ መንፈሳዊ ጸሎት መሸጋገር ለምልጃ ወሳኝ እርምጃ ነው።
6. ወደ ምልጃ እግዚአብሔር ፍሬያማ ምልጃ እንደሚሰጠን እያመንን ልናመሰግነው ይገባል። እግዚአብሔር ከማንነቱና ከባሕሪው የተነሣ ጸሎታችንን ውጤታማ እንደሚያደርገው በማመን እናመስግነው።
7. በመጠባበቅ መንፈስና ከእርሱ ምሪትን ለመቀበል በፊቱ መቆየት እንለማመድ።
    - መዝሙር 62÷5 – **"ነፍሴ ሆይ፤ ዐርፈሽ እግዚአብሔርን ብቻ ጠብቂ፤ ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ነውና።"**
    - ሚክያስ 7÷7 – **"እኔ ግን እግዚአብሔርን ተስፋ አደርጋለሁ፤ አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠብቃለሁ፤ አምላኬ ይሰማኛል።"**
    - መዝሙር 81÷13-14 – **"ምነው ሕዝቤ ቢያደምጠኝ ኖሮ፣ እስራኤል በመንገዴ በሄደ ኖሮ፣ ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባንበረከክኋቸው ነበር፤ እጄን በባላጋራዎቻቸው ላይ ባነሣሁ ነበር።"**
8. በእምነትና በመታዘዝ በምልጃችን ጊዜ እግዚአብሔር ወደ አእምሮአችን የሚያመጣውን ጸሎት እንጸልይ። **"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል"** (ዮሐንስ 10÷27)
    - እግዚአብሔርን እየተጠባበቅን ምሪት እንዲሰጠን እንጠይቀው፤ እርሱም ሊሰጠን የታመነ ነውና። (መዝሙር 32÷8)
    - እግዚአብሔር ሊለን የሚፈልገውን ሁሉ በትዕግሥት ማስጨረስ እንለማመድ። የእምነት አባቶችን ታሪክ ስናይ በመጠብቅም ሆነ ባለመጠበቅ ያገኙትን ውጤት በቃሉ ውስጥ በስፋት ተጠቅሶ እናነባለን።
9. ሁልጊዜ በአጠገባችሁ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ልናደርግ ይገባል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ የሚናገረንና የሚያረጋግጥልን በቃሉ ነውና። (መዝሙር 119÷10-15)
10. እግዚአብሔር በመንፈሳችን የሚያፈሰው ሸክም ሲያበቃ እኛም ጸሎታችንን ስላደረገው ሁሉ በማመስገንና ራሱን በማድነቅ የምልጃ ጊዜያችንን እንጨርሳለን ማለት ነው። **"ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"** (ሮሜ 11÷36)

# ስለምን እንማልድ?

የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ምን መማለድ እንደሚገባን ያመለክቱናል፦

| | |
|---|---|
| • ለኢየሩሳሌም ሰላም | መዝሙር 122÷6 |
| • ለመከሩ ሠራተኞች እንዲላኩ | ማቴዎስ 9÷38፤ ሉቃስ 10÷2 |
| • ወደ ፈተና እንዳንገባ | ሉቃስ 22÷40-46 |
| • ለሚበድሉአችሁ ጸልዩ | ሉቃስ 6÷28 |
| • ለቅዱሳን ሁሉ | ኤፌሶን 6÷18 |
| • ለጎሙማን | ያዕቆብ 5÷14 |
| • አንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከም | ያዕቆብ 5÷16 |
| (ለሌሎች ባለመጸለይ እግዚአብሔርን እንበድላለንና) | 1ኛ ሳሙኤል 12÷23 |
| • ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለሥልጣናት | 1ኛ ጢሞቴዎስ 2÷1-4 |
| • ለዕለት እንጀራ | ማቴዎስ 6÷11 |
| • ለጥበብ | ያዕቆብ 1÷5 |
| • ለፈውስ | ያዕቆብ 5÷14-15 |
| • የእግዚአብሔር ፈቃድና መንግሥት እንዲሰለጥን | ማቴዎስ 6÷10 |
| • ለክርስቶስ አካል የመንፈስ አንድነት | ዮሐንስ 17 |
| • ለምትሰደደው ቤተክርስቲያን | ዕብራውያን 13÷3 |

# ተስፋዎች ለምልጃ

እግዚአብሔር ጸሎትን የሚመልሰው እንደፈቃዱ ሲቀርብ ነው። ፈቃዱ ደግሞ በቃሉ ላይ የሰጠንን ተስፋዎች ተጨባጭ የሚያደርግ ነው። ጸሎታችን በተስፋ ቃሎች ላይ የተመሠረተ ካልሆነ ፍሬ ቢስ ይሆናል።

> ***"ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና።"*** (ያዕቆብ 4÷3)

- በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው የጸሎት ግንኙነት ልክ በወላጅና በልጆች መካከል እንዳለው ዓይነት ይመስላል። ማንም ወላጅ ቢሆን ልጆቹ የጠየቁትን ሁሉ አይሰጣቸውም። አንዱን ሊፈቅድ ሌላውን ደግሞ ሊከለክል ይችላል። በዚህ ድንበር ውስጥ ነው አባት የልጁን ጥያቄ የሚመልሰው።
- በእግዚአብሔርም ዘንድ እንዲሁ ነው። እርሱ ተስፋዎችን ሰጥቶናል፤ እነዚህ ተስፋዎች ደግሞ ለጸሎታችን ድንበር ወይም ገደብ ናቸው። ለዚህ ነው በቃሉ ላይ የተሰጡንን ተስፋዎች በሚገባ ልናጠናቸው የሚገባን።

- ለዚህ አንዱ የሚረዳን ነገር መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከዘፍጥረት እስከ የዩሐንስ ራእይ ድረስ ስናጠና የምናገኛቸውንና እንደ አማኝና እንደ ቤተክርስቲያን የተሰጡ ተስፋዎን እያሰመርንባቸው፣ በጸሎታችን ጊዜ እንጠቀምባቸው።
- እንደ ተስፋ ቃሉ ስንጸልይ፣ እግዚአብሔርን መልሰን በቃሉ እያናገርነው ነው ማለት ነው። ለምሳሌ፡- **"ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤ 'መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።' "** (ማቴዎስ 9፥37-38)
- እነዚህንም ተጨማሪ ጥቂት ተስፋዎችን እንመልከት። እነዚህ ተስፋዎች በቀጥታ በጸሎት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡-
  - አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃል — ማቴዎስ 6፥8
  - ከእናንተ ሁለቱ ቢስማሙ እኔ እመልሳለሁ — ማቴዎስ 18፥19
  - ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል — ማቴዎስ 19፥26፤ ሉቃስ 18፥27
  - ጸሎት ከእምነት ጋር ፍሬያማ ነው — ማቴዎስ 21፥22፤ ማርቆስ 11፥24
  - በስሜ የምትለምኑትን አደርገዋለሁ — ዩሐንስ 14፥14
  - የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች — ያዕቆብ 5፥16

## ማስታወሻ

# ክፍል 5
# የምልጃ ጸሎት እንቅፋቶች

---

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፦

- የምልጃ እንቅፋቶችን መለየትና ማስወገድ
- መቼ መጸለይ እንደሌለብን ማወቅ

## ቁልፍ ጥቅስ፦

*"ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና።"*
(ያዕቆብ 4፥3፤ አ.መ.ት.)

## *መግቢያ*

የምልጃን ጸሎት በሚገባ ማከናወን ከፈለግን፣ ለምልጃ እንቅፋት የሚሆኑትን ነገሮች ለይተን ከሕይወታችን ማስወገድ ይኖርብናል። *"እንቅፋት"* ስንል ፍሬያማ የምልጃ አገልግሎት እንዳይኖረን በመካከል የሚገቡት መሰናክሎችን ማለታችን ነው።

## *የምልጃ እንቅፋቶች ምንድን ናቸው?*

የምልጃ እንቅፋቶችን እንድንለይ የሚረዱንን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች እናጥና።

| | |
|---|---|
| • ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት | ኢሳይያስ 59፥1-2፤ መዝሙር 66፥18 |
| | ኢሳይያስ 1፥15፤ ምሳሌ 28፥9 |
| • ጣዖት የሆኑብን ነገሮች | ሕዝቅኤል 14፥1-3 |
| • ይቅር ያለማለት መንፈስ | ማርቆስ 11፥25፤ ማቴዎስ 5፥23 |
| • እኔነትና ጤናማ ያልሆነ ስውር አሳብ (Wrong Motive) | ምሳሌ 21፥13፤ ያዕቆብ 4፥3 |
| • ተወዳዳሪ መንፈስ፣ የሌላውን ሰው አሳብ ለማስለወጥ የሚጸለይ ጸሎት | ያዕቆብ 4፥2-3 |
| • ከትዳር ጓደኛ ጋር ያለ የሻከረ ግንኙነት | 1ኛ ጴጥሮስ 3፥7 |
| • የራስ ጽድቅ (ፈሪሳዊውና ቀራጩ) | ሉቃስ 18፥10-14 |
| • አለማመን | ያዕቆብ 1፥6-7 |
| • በክርስቶስ አለመኖርና ቃሉ በእኛ አለመኖሩ | ዩሐንስ 15፥7 |

| | |
|---|---|
| • ርኅራኄ ማጣት | ምሳሌ 21÷13 |
| • ግብዝነት፣ ትምክህተኛነት፣ ትርጒም የሌለው ድግግሞሽ | ማቴዎስ 6÷5፤ ኢዮብ 35÷12-13 |
| • እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አለመጸለይ | ያዕቆብ 4÷2-3 |
| • በክርስቶስ ስም አለመጸለይ | ዮሐንስ 16÷24 |
| • ዲያቢሎስና አጋንንቶቹ የሚያመጧቸው እንቅፋቶች | ዳንኤል 10÷10-13፤ ኤፌሶን 6÷12 |
| • አስቀድመን መንግሥቱን አለመፈለግ | ማቴዎስ 6÷33 |
| • የመንፈስ ቅዱስን ምሪት አለመሻት | ሮሜ 8÷26 |

### የምልጃን እንቅፋቶች ማስወገድ

የምልጃን እንቅፋት መረዳት የመፍትሔው መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይደለም። ስለዚህ እነዚህ እንቅፋቶች እንዲወገዱ፡-

- እግዚአብሔር እንዲያስወግድልን በጸሎት እንጠይቀው።
- የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን እንሰውር፤ ለመሰወር ደግሞ ቃሉን እናንብብ፣ እናጥና፣ እናሰላስልና እንታዘዝ።
- መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳን እንጠይቀው።

በዚህ ውስጥ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ቢኖር ያልተመለሰ ጸሎት ሁሉ በሕይወታችን ከሚገጥሙን ከእነዚህ እንቅፋቶች ብቻ የተነሣ ነው ማለት አይደለም። በክፍል አንድ ትምህርታችን እንደተማርነው፡-

- አንዳንድ ጊዜ የጸሎት መልስ ይዘገያል (ሉቃስ 18÷7)
- እንዲሁም ከጠየቅነው የተለየ መልስ ሊመጣ ይችላል (2ኛ ቆሮንቶስ 12÷8-9)

## መቼ መጸለይ እንደሌለብን ማወቅ

ሁልጊዜ መጸለይ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲመራንና እንዲያሳየን በፊቱ መቆየት መለማመድ አስፈላጊ የምልጃች ጸሎት ክፍል ነው። መጸለይ ተገቢ እንደሆነ ሁሉ መቼ ደግሞ አለመጸለይ እንደሚገባን ልንረዳ ያስፈልጋል። አንዳንዴ ስንማልድ ቆይተን እግዚአብሔር እንዲናገር እድል ስንሰጠው፣ ተጨማሪ ጸሎት ሳይሆን ተግባራዊ እርምጃ እንድንወስድ ሊያመለክተን ይችላል።

ይህንን እንድንገነዘብ የሚረዱንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን እንመልከት፡-

- በዘጸዓት ምእራፍ 15 እናነባለን። እስራኤላውያን በምድረበዳ ከሦስት ቀን ጥም በኋላ ወደ ማራ መጡ፤ በዚያም ያገኙት ውሃ መራራ ነበርና መጠጣት አልቻሉም። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር በጮኸ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ውሃውን ለማጣፈት ምን ማድረግ እንደሚገባው መራው። ከዚህ በኋላ ስለ ጉዳዩ መጸለይም ሆነ እግዚአብሔርን

መጠበቅ አላስፈለገውም ነበር። ይልቁንም እርምጃ መውሰድ ነበረበት ስለዚህ እግዚአብሔር ያሳየውን እንጨት በውሃ ውስጥ ጣለውና ጣፈጠ።

- ኢያሱም በጋይ እስራኤል በጠላቶቻቸው ሲመቱ ተመሳሳይ ነገር ገጥሞታል። እግዚአብሔር በመካከላቸው እርም እንዳለ ገለጠለት። ***"እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፤ "ተነሥ! ለምን በግንባርህ ተደፋህ? እስራኤል በድሎአል፤ እንዲጠብቁ ያዘዝኋቸውን ቃል ኪዳኔን ጥሰዋል፤ እርም የሆነውን ነገር ወስደዋል፤ ሰርቀዋል፤ ዋሽተዋል፤ የወሰዱትንም ከራሳቸው ንብረት ጋር ደባልቀዋል። እንግዲህ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ለመቋቋም ያልቻሉት በዚህ ምክንያት ነው። ጀርባቸውን አዙረው የሸሹትም ለጥፋት በመዳረጋቸው ነው። እርም የሆነውን ነገር ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ፣ ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም።"*** (ኢያሱ 7፥10-12)
    - እግዚአብሔር ከተናገረ በኋላ የጸሎት ጊዜ ሳይሆን የእርምጃ ጊዜ ነበር።
    - የምልጃ ጸሎት ጌታ የሚለውን እንዳንታዘዝ የምንደበቅበት ዋሻ መሆን የለበትም።
    - ኃይለኛ ምልጃ ልዩነት ወደሚፈጥር እርምጃ ይመራናል።
    - አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር ምልጃውን መልሶ ጸሎታቸውን ይቀጥላሉ፤ ምክንያቱም መልሱን አልወደዱትምና።
- በዘኁልቁ ምእራፍ 22 ላይ ደግሞ ባላቅ በለአምን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ጠይልቅኝ አለው። በለአምም እግዚአብሔር ያለውን ነገረው። ነገር ግን ባላቅ ደጋግሞ ባለሥልጣናትን እየላከ እግዚአብሔርን ደግመህ ጠይቅልኝ ሲለው፣ በለአም እንዲህ አለ፦ ***"በለዓም ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ 'ሌላው ይቅርና ባላቅ በብርና በወርቅ የተሞላ ቤተ መንግሥቱን ቢሰጠኝ እንኳ፣ የአምላኬን የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) ትእዛዝ በመጣስ ከዚያ ያለፈ ወይም ያነሰ ማንኛውንም ነገር ማድረግ አልችልም። አሁንም ሌሎቹ እንዳደረጉት ሁሉ፣ እናንተም ዛሬ እዚሁ ዕደሩና እግዚአብሔር (ያህዌ) ምን እንደሚለኝ ደግሞ ልወቅ።' በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወደ በለዓም መጥቶ፣ 'እነዚህ ሰዎች የመጡት እንድትሄድላቸው እስከ ሆነ ድረስ አብረሃቸው ሂድ፤ ነገር ግን እኔ የምነግርህን ብቻ አድርግ።'"*** (ከቁጥር 18-20)

# ማስታወሻ

# ክፍል 6
# ጌታ ያስተማረን ጸሎት ለምልጃ

*በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፦*

- *ጌታ ደቀመዝሙርትን ያስተማረቸው በእርግጥም የምልጃ ጸሎት መሆኑን*
- *ይህንን ጌታ ያስተማረንን ጸሎት ለምልጃ መርህ አድርጎ መጠቀም*

## ቁልፍ ጥቅስ፦

***"እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤***
***'በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤***
***ስምህ ይቀደስ፤***
***መንግሥትህ ትምጣ፤***
***ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች፣***
***እንዲሁ በምድር ትሁን።***
***የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።***
***እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣***
***በደላችንን ይቅር በለን።***
***ወደ ፈተናም አታግባን***
***ከክፉው አድነን እንጂ፣***
***መንግሥት፣ ኃይል፣ ክብርም፣***
***ለዘለዓለሙ ያንተ ነውና፤ አሜን።'"*** (ማቴዎስ 6፥9-13፤ አ.መ.ት.)

## መግቢያ

ጌታችን ያስተማረው ጸሎት በአዲስ ኪዳን በሁለት ወንጌላት ተጠቅሶ እናገኘዋለን፤ በማቴዎስ 6፥9-13 እንዲሁም በሉቃስ 11፥2-4። በማቴዎስ ላይ የተጠቀሰበትን ወቅት ስናይ የተራራው ስብከት በመባል በሚታወቀው ታሪክ ውስጥ አብሮ ተካቶአል። ይሁን እንጂ ሉቃስ የዘገበው ጌታ አገልግሎቱን ከጀመረ ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ ደቀመዛምርቱ መጥተው እንደጠየቁት ነው። በዚህ ጊዜ ደግሞ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ሲጸልይ በርካታ ጊዜ አይተውታል፤ በተጨማሪም የጸሎቱን ውጤት ያስገኘውን ኃይል በሚገባ ተለማምደዋል። ይህም በውስጣቸው ለጸሎት ከፍተኛ ጥማት ስላስነሳ፦ **"እንዴት እንደምንጸልይ አስተምረን"** ብለው ጌታን ለመጠየቅ አብቅቷቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ ጌታ ከላይ የተጠቀሰውን ክፍል **"ስትጸልዩ …"** በማለት አስተማራቸው።

## ይህ ጸሎት የምልጃ ጸሎት ነው

- የደቀመዛሙርቱ ጥያቄ *"መጸለይ አስተምረን"* እንጂ *"ጸሎት"* አስተምረን የሚል ጥያቄ አይደለም። **"ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ "ጌታ ሆይ፤ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ጸሎት እንዳስተማራቸው አንተም መጸለይን አስተምረን" አለው።"** (ሉቃስ 11፥1)
- ጌታም ያስተማራቸው የአይሁድ መምህራን ሲጠቀሙትበት በነበረው መንገድ ነው። ይህም፡-
  - የአይሁድ መምህራን መጀመሪያ በእውነት ላይ የተመሠረቱ ርዕሶች ይዘረዝራሉ
  - ለእያንዳንዱ ጸሎት ዋና ዋና አሳብ ያወጣሉ (Prayer Outline)
  - በእያንዳንዱ ርዕስ ላይ ይጸልያሉ
- ይህንን ጸሎት የምልጃ ጸሎት እንደሆነ የሚያመለክተው ከጅማሬው አንስቶ **"አባታችን"**፣ **"ስጠን"**፣ **"አታግባን"**፣ **"ይቅር በለን"** የሚሉት ቃላቶች ናቸው። ጸሎቱ የግል ሳይሆን ከራስ ያለፈ መሆኑ ያሳያል።

## ጌታ ያስተማረው ጸሎት በዝርዝር

### በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ

- **"አባታችን ሆይ"** የሚለው ቃል ቅርበቱን፤ **"በሰማያት የምትኖር"** የሚለው ደግሞ ርቀቱን የሚያመለክት ይመስላል።
- መዝሙር 139 ግን እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ መሆኑን ይነግረናል። ይህ ከሆነ **"በሰማያት የምትኖር"** የሚለው በእኛና በአባታችን መካከል ያለውን ርቀት ለማመልከት ሳይሆን ከሚታየው ዓለም ባሻገር ወደማይታየውን ዓለም እኛን ፈጥኖ ለማምጣት ነው።
- እንዲህ ስንጸልይ የምልጃችን ምላሽ ምንጩ መንፈሳዊ መሆኑን የሚያስረግጥልን ነው።
- "አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር" ስንል በክርስቶስ ኢየሱስ ከሰው ችሎታ ከሚያልፈውና ገደብ የሌለው ምንጭ ከሆነው አባታችን እግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ተገናኝተን ነው ወደ ምልጃ የምንገባው።

### ስምህ ይቀደስ

የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ስንሆን፣ የሰማዩ አባታችን በስሙ እንድንጠራ ፈቅዶአል። ይህም ማለት አንድ ልጅ ለአሳዳጊ ሲሰጥ የአዲሱን አባት ስም እንደሚወስድ ሁሉ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን እርሱን "አባ" ብለን ለመጥራት ሙሉ መብት ይሰጠናል፤ በተጨማሪም ከአባትነቱ ጋር የሚመጣውን በረከት ሁሉ ለመቀበልና ለመውረስ ብቁ ያደርገናል።

የእግዚአብሔር ስም መጠሪያ ብቻ ሳይሆን የባሕሪውና የማንነቱ መገለጫ ነው። **"ስምህ ይቀደስ"** ስንል ማንነቱን፣ ኃይሉንና ሥልጣኑን ነው የምናውጀው። ለምሳሌ የሚከተለውን ዓይነት ጸሎት በዚህ መረዳት ሆኖ መጸለይ ይቻላል፡-

**"ለወንድሜ <u>የሰላም አምላክ</u> እንድትሆነው እጸልያለሁ። <u>ሰጪ የሆንክ እግዚአብሔር</u> በወንድሜ መሠረታዊ ፍላጐቶች ላይ በቸርነትህ እንድትመጣ እጠይቅሃለሁ። አላማዬ የሆንክ እግዚአብሔር በወንድሜ ሕይወት ላይ እንድትነግሥ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ የምትቀድስ እግዚአብሔር እንደሆንህ ሁሉ የወንድሜን ሕይወት እንድትቀድስ እቃትታለሁ። ወዘተ …"**

የሚከተለው ዝርዝር ሰባቱን የእግዚአብሔርን ውህድ ስሞችና ትርጉሞቻቸውን ያስተምረናል፦

| ስም | ትርጉም | ጥቅስ |
|---|---|---|
| ያህዌ ጽድቅኑ | እግዚአብሔር ጽድቃችን | ኤርምያስ 23÷6 |
| ያህዌ መቃዴሽ | እግዚአብሔር የሚቀድስ | ዘጸዓት 31÷13 |
| ያህዌ ሻሎም | እግዚአብሔር ሰላም ነው | መሳፍንት 6÷24 |
| ያህዌ ሻማህ | እግዚአብሔር በዚያ አለ | ሕዝቅኤል 48÷35 |
| ያህዌ ሮፌ | እግዚአብሔር ፈዋሽ | ዘጸዓት 15÷16 |
| ያህዌ ጃይረ | እግዚአብሔር ሰጪአችን | ዘፍጥረት 22÷14 |
| ያህዌ ኒሲ | እግዚአብሔር ዓላማዬ | ዘጸዓት 17÷15 |
| ያህዌ ሮዒ | እግዚአብሔር እረኛዬ | መዝሙር 23÷1 |

## መንግሥትህ ትምጣ

- በዕብራይስጥ፣ በግሪክና በአረማይካ "መንግሥት" የሚለው ቃል ንግሥና፣ ግዛት፣ ማስተዳደር ወይም የእግዚአብሔር ገዢነት በማለት ይተረጉሙታል።
- የእግዚአብሔር መንግሥት ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል፦
  - ፍጥረትን ሁሉ ጠቅሎል የሚገዛው እግዚአብሔርና መላእክቱን።
  - በሚታየው አለም ውስጥ መንግሥቱ የሚገለጥባት አካል ቤተክርስቲያንን።
  - በዚያ ውስጥ የምንካተተው አማኞችን።
- አንድ ቀን የእግዚአብሔር መንግሥት ሁሉንም ድል ነሥታ በገሃድ ትገለጣለች። የዓለም መንግሥታት ለእግዚአብሔር ተንበርክከው፤ የሰይጣንም መንግሥት ሙሉ በሙሉ ተንኮታኩቶ ጌታችን በምድር ላይ ይነግሣል። (ራእይ 11÷15)
- የእግዚአብሔር መንግሥት የወንጌሉ መካከለኛ መልእክት መሆኑ ግልጥ ነው። 49 ጊዜ በማቴዎስ ላይ፣ 16 ጊዜ በማርቆስና 38 ጊዜ በሉቃስ ወንጌል ላይ ተጽፎአል።

- ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን የጀመረው፦ **"የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች"** በማለት ነበር (ማቴዎስ 4፥17)።
- በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎቱን ያጠናቀቀው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በመናገር ነበር (የሐዋሪያት ሥራ 1፥3)።
- የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልክትና ምሳሌዎች በአብዛኛው የሚያጠነጥኑት በእግዚአብሔር መንግሥት ዙሪያ ነበር። **"እርሱ ግን፣ "ወደ ሌሎቹም ከተሞች ሄጄ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል መስበክ ይገባኛል፤ የተላክሁት ለዚሁ ዐላማ ነውና" አላቸው።"** (ሉቃስ 4፥43)
- እኛም አማኞች ለሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንግሥቱ አትኩሮት እንድንሰጥ ያሳስበናል፦
**"ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል።"** (ማቴዎስ 6፥33)
- ይህ ጥቅስ ጸሎታችን፣ ስብከታችን፣ አስተምህሮቶቻችንና ሕይወታችን በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ያመለክታል። መንግሥቱን አስቀድመው የሚሹ ሁሉ ውጤታማ የሆነ ምልጃ አገልግሎት ሊማካሄድ ይችላሉና።
- **"መንግሥት ትምጣ"** የሚለው ጸሎት በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ከመወሰን ያለፈ ጸሎት ነው። ምክንያቱም **"መንግሥትህ ትምጣ"** እያልን ስንጸልይ አባታችን በሚያምኑ፣ በማያምኑና በፍጥረተ ዓለሙ ላይ ግዛ እያልን ማወጃችን ጭምር ነው። ለእግዚአብሔር ገዢነት እውቅና መስጠታችን ነው።
- **"መንግሥትህ ትምጣ"** ስንል በውስጣችን ሆነ በሌሎች ያለ የአመጻኝነትን ቃል፣ መንፈስ፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ባሕሪ ... ወዘተ. አስወግደህ ግዛ እያልነው ነው።

## ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች፣ እንዲሁ በምድር ትሁን

- በግሪኩ ላይ **"ፈቃድህ"** የሚለው ሁለት ፍቺ አለው፦
    - <u>የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ (Perfect Will of God) (Greek – boulema)</u> – ይህ ፈቃዱ በምንም ዓይነት ሁኔታ የማይታጠፍና የማይለወጥ ፈቃድ ነው። ይህም እግዚአብሔር በዘላለም አሳቡ ያቀደው ፈቃዱ ነው። **"ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል"** (ኤፌሶን 1፥11) እግዚአብሔር ለማዳን የመረጠው መንገድ የማይለወጥ መሆኑን ያሳያል።
        - ይህ ፈቃዱ የሰውን ትብብር አይጠይቅም። ውጤቱ የታወቀና የተወሰነ ነውና። ይህ ፈቃዱ የተጻፈና በቃሉ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ነው። በዚህ ዙሪያ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ እግዚአብሔር መጠየቅ የለብንም፤ በቃሉ ላይ በግልጽ ተጽፎአልና።
    - <u>በሰው ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የእግዚአብሔር ፈቃድ (Permissive Will of God) (Greek – thelema)</u> – እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ያለውን እቅድና ፈቃድ የሚመለከት ነው። ይህ ፈቃዱ ለመከናወን የሰውን ትብብር ይጠይቃል። በዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመኖር ምርጫው የግለሰቡ ነው። በራሳችን ላይ ሆነ በሌሎች ላይ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ብለን ስንጸልይ ይህንን ዓይነቱን ፈቃድ ነው የምንጸልየው።

### የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን

- ጌታ ባስተማረን ጸሎት መሠረት በመጀመሪያ መንግሥቱን ፈለግን፣ በመቀጠልም መንግሥቱን በሁኔታችን ሁሉ ላይ ጠራን። ፈቃድህ ትሁን በማለታችን ለእግዚአብሔር ጽድቅ ራሳችንን እናስገዛለን። ከዚህ በኋላ በሙሉ ልብ የዕለት እንጀራችንን ስጠን እያልን ፈቃዱን ለማድረግ እንዲያስችለን መጸለይ እንችላለን።
- **"ስጠን"** ብለን ስንጸልይ እግዚአብሔር ደሞዝ ከፋይ ሳይሆን ምንጭ ለመሆኑን እውቅና የሚሰጥ ነው።
- በዚህ ጸሎት ውስጥ "እንጀራችንን" የሚለው የግሪኩ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ሥፍራ አልተጠቀሰም። ትርጉሙም፦ የሚያስፈልግ፣ ወሳኝ የሆነ፣ ለመኖር በቂ የሆነ የሚል ነው። ይህ ጸሎት በየዕለቱ ቀጣይ የሆነ ጸሎት እንደሆነም ያመለክታል።
- ጸሎቱ ስለ **"እንጀራ"** ነው። እንጀራ ስንል ደግሞ ለመንፈስም ለአካልም የሚያስፈልገውን ይጠቀልላል። "ስጠን" ማለቱ ደግሞ ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚጸለይ ጸሎት መሆኑን ያመለክታል።

## እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን

በግል ሕይወታችንና በሰዎች አማካኝነት ለደረሱብን ጥቃትና የፍርድ መዛባት ይቅርታን መቀበልና መስጠት ልንማር ይገባል፤ ማለትም እኛ እግዚአብሔርን ስናስቆጣና ሰዎች እኛን ሲያጠቁን። ስለዚህ **"በደላችንን ይቅር በለን"** ስንል እነዚህን ያጠቃልላል። በ፲ኛ ዮሐንስ ፩÷8-9 እንዲህ ይላል፦

> **"ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው።"**

እኛ የምናውቀውን ኃጢአት ስንናዘዝ፣ እግዚአብሔር ደግሞ የተናዘዝነውንና ባለማወቅ ያልተናዘዝነውን ኃጢአት ጭምር ይቅር በማለት ከእርኩሰት ሁሉ ያነጻናል።

ይቅር የማለት ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ሌሎችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለበደሉን በደል የምንሰጠው ይቅርታ ነው። ቀጥታ የምንለው በእኛ ላይ የሚደርሰውን በደል ሲሆን፣ በተዘዋዋሪ ስንል ደግሞ ዘመድ፣ ወገን ወይም ጓደኛ ላይ ከሚደርሰው በደል የተነሣ እኛም እንደተበደልን ሲሰማን ማለት ነው። እነዚህን ሁሉ ይዘን በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ማስተካከል ይኖርብናል።

ጌታ ያስተማራቸው ጸሎት በግሪኩ ጽሑፍ በቀጥታ ሲነበብ "እኛም የበደሉንን ይቅር እንዳልን" ነው የሚለው - ይቅር "እንደምንል" ሳይሆን "እንዳልን"። ስለዚህ ይቅርታን ለመጠየቅ ወደ እግዚአብሔር ፊት ከመምጣታችን በፊት የበደሉንን ይቅር ብለናል ማለት ነው። በማቴዎስ ፲8÷22-35 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምረን፣ የእግዚአብሔር ይቅርታ የእኛን ይቅርታ ማድረግ ይቀድማል። ምክንያቱን የእኛ ይቅር ማለት የእግዚአብሔር እኛን የመማሩ ነጸብራቅ ነውና። ታዲያ የእግዚአብሔር ይቅርታ ለእኛ ሕይወት የሚሆነን ሌሎችን ይቅር ለማለት ስንፈቅድ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን እውነት እንዲህ ያጠቃልለዋል፦

> **"እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ። ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር አይለችሁም።"** ማርቆስ 11÷25-26

ሰይጣን በቤተሰብ ውስጥ፣ በጓደኞች መካከል፣ በሥራ ቦታና በቤተክርስቲያን ውስጥ ጥቃትን ይቀሰቅሳል። መጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ 18÷7 ላይ እንዲህ ይላል፡- **"ይህች ዓለም የመሰናክል ምክንያት በመሆኗ ወዮላት! መሰናክል መምጣቱ አይቀርምና፤ ነገር ግን የመሰናክሉ ምክንያት ለሚሆነው ሰው ወዮለት።"** እንዲህ ያለ ችግሮች በሚገጥሙን ጊዜ በምልጃ በእግዚአብሔር ፊት እንቀርባለን ወይስ ሐሜትን አማርጭ አድርገን እንነሣለን?

## ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉው አድነን እንጂ

ጌታችን **"ወደ ፈታናም አታግባን"** የሚለውን ጸሎት ሲያስተምረን፣ ያዕቆብ ደግሞ እግዚአብሔርን ሰውን በክፉ እንደማይፈትን ያስተምራል፡-

> **"ማንም ሲፈተን፣ 'እግዚአብሔር ፈተነኝ' አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም"** - ያዕቆብ 1÷13

ታዲያ ኢየሱስ የሚጠቅሰው ፈታኝ ማነው? ይህ ሥራ የዲያቢሎስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ያረጋግጥልናል (ማቴዎስ 4÷3፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 3÷5)። ቅዱሳን መጻሕፍት በተደጋጋሚ ከሰይጣን ስለሚመጣው ፈተና ያስጠነቅቁናል (ማቴዎስ 4÷1፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 7÷5፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 3÷5)። መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስረዳ፡-

> **"ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። 15ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።"** – ያዕቆብ 1÷14-15

ሰይጣን ፈታኝ ቢሆንም የምንፈተነው በምኞታችን ስንሳብና ስንታለን ነው። እንደነዚህ ያሉ የሥጋ ምኞቶች ኃጢአትን ይወልዳሉ፤ ይህም ውጤቱ ሞት ነው። አንዳንዶቹ የጠላት ጥቃቶችን የሚነሱት ራሳችንን ባለመግዛት በውስጣችን ካለ ክፉ ምኞት የሚቀሰቀስ ሲሆን ሌላው ደግሞ ÷ መስማትን፣ ማየትን፣ መንካትን፣ ማሽተትን፣ መቅመስን በመጠቀም የሚጣብን ውጫዊ የጠላት ጥቃት ነው። ከየትኛውም ምንጭ ጥቃት ቢነሳም፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያረጋግጥልናል፡-

> **"በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።"** – 1ኛ ቆሮንቶስ 10÷13

“ወደ ፈተና አታግባን” ብለን ስንጸልይ፣ ከሚነሱብን የኃጢአት ማባበያዎች ጠብቀን እያልን ነው። ኢየሱስ እንኳን ከፈተናው ባይጠበቅም፣ በፈተና ውስጥ ግን ተጠብቆ ነበር። **“በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሠራም።”** (ዕብራውያን 4፥15)። ሐዋሪያው ዩሐንስም ጨምሮ ያረጋግጥልናል፦

> **“ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአት እንደማያደርግ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚጠብቀው፣ ክፉውም እንደማይነካው እናውቃለን።”** – 1ኛ ዩሐንስ 5፥18

በኤፌሶን 6፥10-18 ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ ክፉውና እርሱን ስለምንዋጋበት መንፈሳዊ መሣሪዎች በዝርዝር ያስረዳል። ሐዋሪያው በእግዚአብሔር ኃይል ችሎት አጥብቀን እንድንበረታ፣ ክፉውን ለመቃወም ጸንተን እንድንቆም በጥብቅ ያሳስበናል። የጠላትን ተንኮል፣ አታላይነትና ብልሃት መቃወም የሚቻል ነገር መሆኑን ለአማኞች ያውጃል። መልካሙን ገድል እንድንጋደል (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥18)፣ የእምነትን ገድል እንድንጋደል (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥12)፣ እንዲሁም በዓላማ እንድንታገል (1ኛ ቆሮንቶስ 9፥26) ያበረታታናል።

ከዚህም በተጨማሪ ሐዋሪያው ጳውሎስ ውጊያችን በሚታየው አለም ውስጥ አለመሆኑን፣ መሣሪያዎቻችንም ሥጋዊ እንዳልሆኑ ይልቁንም ውጊያው በመንፈሳዊ መሣሪያዎች በመንፈስ የምንዋጋ ስለመኑ ይናገራል። (ኤፌሶን 6፥13-18)

የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር የሚያስፈልግበት ዋነኛው ምክንያት የዲያብሎስን የተንኮል ሥራ ለመቋቋም እንድንችል ነው። ቃሉ **“የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ”** ሲል የእኛ ኃላፊነት መሆኑን ያስገነዝበናል። መልበስ ማለት አንድን ነገር ማንሣትና መጠቀምን ያመለክታል። በየዕለቱ ለሌሎችና ለራሳችን ስንጸልይ በሚከተሉት መንገዶች ልንማልድ እንችላለን፦

| **ዕቃ ጦር** | **ማወጅ** | **የተስፋ ቃል** | **የሚታሠር መንፈስ** |
|---|---|---|---|
| በእውነት ዝናር የታጠቀ ወገብ | ኢየሱስ ፥ አንተ እውነት ነህ | ዩሐንስ 14፥6 | አታላይ መንፈስ |
| የጽድቅ ጥሩር | ኢየሱስ ፥ አንተ ጽድቄ ነህ | 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥21 | የርኩሰት መንፈስ |
| በሰላም ወንጌል ዝግጁነት የተጫማ እግር | ኢየሱስ ፥ አንተ ኃይሌ ነህ | ፊልጵስዩስ 4፥13 | የሚጫጫን መንፈስ |
| የእምነት ጋሻ | ኢየሱስ ፥ አንተ እምነቴ ነህ | ገላትያ 2፥20 | አለማመንና ጥርጣሬ |
| የመዳን ራስ ቍር | ኢየሱስ ፥ አንተ ድኅነቴ ነህ | ዕብራውያን 5፥9 | ክፉ አሳብን የሚዘራ |
| የመንፈስን ሰይፍ | ኢየሱስ ፥ አንተ ሕያው ቃል ነህ | ዩሐንስ 1፥14 | የጠላትን ውሸት |

## *መንግሥት፣ ኃይል፣ ክብርም፣ ለዘለዓለሙ ያንተ ነውና*

"ነውና" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጌታ ያስተማረንን ጸሎት በምን ሥልጣን እንደምንጸልይ ያመለክታል። ይህም ማለት ከመንግሥቱ ኃይልና ክብር የተነሣ የጌታን በረከቶች፣ ተስፋዎችና ጥበቃ ልንጠይቅ እንችላለን። ወደ ጸሎቱ ማጠቃለያ ስንመጣ "መንግሥት ያንተ ናት" ከሚለው መልእክት ጋር ሙሉ በሙሉ መስማማታችንን እየገለጥን ነው።

> ***"እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ መልካም ፈቃድ ነውና አትፍሩ"*** – ሉቃስ 12÷32

የእግዚአብሔር መንግሥት ነው፣ እንደወራሽ ግን የእኛም መንግሥት ነው። ይህ ውርስ ወይም ቅርስ በዘላለም ምክሩ ለእኛ ሊሰጠን የወደደው ነው።

በዚህ ጥቅስ ላይ "ኃይል" ብሎ የሚጠራው "ዱናሚስ" የሚለውን ቃል ነው። ይህ ቃል ደግሞ ተወርዋሪ ወይም ድማሚት የሚለውን ትርጉም የያዘ ነው (Dynamic)። ጸሎታችንን ስናጠቃልል እንደ ድማሚት በሆነውን ኃይሉ በመሥራት ለምልጃችን መልስ ይዞ እንደሚመጣ በማመን ነው። "ኃይል የአንተ ነው" ስንለው ክርስቶስ ያለው ቃል በጆሮአችን ያስተጋባል፦ ***"እንግዲህ እባቡንና ጊንጡን እንድትረግጡ፣ በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም።"*** – ሉቃስ 10÷19።

ቀጥለን ደግሞ "ክብርም ያንተ ነው" ብለን እናውጃለን። ክብር (Glory) የሚለውን ቃል በአንድ ቃል ለመተርጐም አይቻልም። ይልቁን የሚከተሉት ቃላት በሕብረት በተወሰነ ደረጃ ይገልጡታል፦ ማክበር (Honor)፣ ግርማ፣ ኃይል፣ ውዳሴ፣ የተገባው፣ ውብ፣ የታወቀና ከፍ ያለ። ኢየሱስ እንዲህ አለ፦

> **"እኛ አንድ እንደሆንን እነርሱም አንድ እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ።"** – ዮሐንስ 17÷22

እግዚአብሔር አብ ክርስቶስን ያከበረበትን ያንኑ ክብር ነው ወልድ ለእኛ የሰጠን። ታዲያ ምን እንዳድርገው? የእኛ ነው ብለን እንመላለስበት። ከዚህ የተነሣ ነው ከውርደት ወደ ውርደት ሳይሆን "ከክብር ወደ ክብር" የምንለወጠው። አንዳንድ ጊዜ ተስፋ ልንቆርጥ፣ በውስጣችን ያለው እሳት ሊቀዘቅዝና መንፈሳዊ ነገር ከውስጣችን የተሚጠጠ ሆኖ ሲሰማን፣ ቃሉ እንዲህ ብሎ ያበረታታናል፦

> **"ብርሃንሽ መጥቶአልና ተነሺ አብሪ፤**
> **የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻል።**
> **እነሆ፤ ጨለማ ምድርን፣**
> **ድቅድቅ ጨለማም ሕዝቦችን ይሸፍናል፤**
> **ነገር ግን እግዚአብሔር ወጥቶልሻል፤**
> **ክብሩንም ይገልጥልሻል።"** – ኢሳይያስ 60÷1-2

የእግዚአብሔር ክብር የሚያረጋግጥልን፦

| | |
|---|---|
| • የሚያስፈልገንን ማግኘት | ፊልጵስዩስ 4፥19፤ ኤፌሶን 3፥16 |
| • ብርታት | ቆላስይስ 1፥11 |
| • ደስታ | ኢሳይያስ 66፥5፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፥8፤ 2ኛ ዜና 16፥10 |
| • ነጻነት | ኢሳይያስ 60፥1 |
| • እረፍት | ኢሳይያስ 11፥10 |
| • መቀደስ | ዘጸዓት 29፥43 |
| • የአካሉን ሕብረት | ዩሐንስ 17፥22 |

**"ለዘላለሙ"** የሚለው ቃል እርሱ በማንነቱ ዘላለማዊ መሆኑንና እኛም ከእርሱ ጋር በክርስቶስ የወረስነው ሕይወት ዘላለማዊ መሆኑን ያሳያል። ይህም በጊዜ ያልተወሰነ አምላክና ጊዜያዊ ለሆነ ሕይወት እኛንም እንዳልጠራን ያሳስበናል።

## አሜን

"አሜን" የሚለውን ቃል ስንጠቀም ጸሎታችንን በታላቅ ኃይል ዐተምነው ማለት ነው። ምክንያቱም "አሜን" አንድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መጠሪያ ነው። **"በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ አሜን የሆነው፣ ደግሞም ታማኝና እውነተኛ ምስክር የሆነው፣ የእግዚአብሔርም ፍጥረት ገዥ የሆነው እንዲህ ይላል"** – ራእይ 3፥14። "አሜን" ስንል ጸሎታችንን በኢየሱስ ስም ጸለይን ማለት ነው።

**"አሜን"** የሚለው ቃል ጨረስን፣ አለቀ ወይም ጸሎታችን አበቃ ማለት አይደለም። ትርጉሙ እንደጸለይኩት እንደዚያው ይሁን ማለታችንና እምነታችንን ማወጃችን ነው።

## ማስታወሻ

# ክፍል 7
# ምልጃ ለመንፈሳዊ ተሃድሶ

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፦

- የመንፈሳዊ ተሃድሶ ፍቺ
- እንዴት ለመንፈሳዊ ተሃድሶ መዘጋጀት እንችላለን
- ተሃድሶ መቼ ነው አስፈላጊ የሚሆነው
- ከመንፈሳዊ ሕይወት የማፈግፈግ ምልክቶች
- ለተሃድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች
- የተሃድሶ እንቅፋቶችን መለየት
- እግዚአብሄር ለተሃድሶ ያለውን ዕቅድ በመጠቀም ለተሃድሶ መማለድ

## ቁልፍ ጥቅስ፦

**"በስሜ የተጠራው ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ፣ ፊቴን ቢፈልግና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ እሰማዋለሁ፤ ኃጢአቱን ይቅር እላለሁ፤ ምድሩንም እፈውሳለሁ።"** (2ኛ ዜና 7፥14፤ አ.መ.ት.)

## መግቢያ

አንዱ የምልጃ ዋነና ተግባር ለተሃድሶ መጸለይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱንን እውነቶች ከእግዚአብሔር ቃል እናጠናለን።

## የተሃድሶ ፍቺ

- አስቀድመን ተሃድሶ ምን እንዳልሆነ እንመልከት።
    - **ተሃድሶ ስሜታዊነት አይደለም።** ሰዎች በተሃድሶ ወቅት ስሜታዊነት ይታይባቸዋል፤ ነገር ግን ስሜት በተሃድሶ ውስጥ ይንጸባረቃል እንጂ ተሃድሶ አይደለም። በእርግጥ እውነተኛ ተሃድሶ የሰዎን ሁለንተና የሚነካ ነው፤ ስሜትንም ጨምሮ። አንድ ተጨባጭ መረጃ ስለተገኘ ብቻ የሰውን ልብ ይነካል ማለት አይቻልም። ለምሳሌ በአልኮል መጠጥ የሞቱ ሰዎች የቁጥር መረጃ አንድ ሰካራም ስላወቀ ስካሩን አይተውም። የወንጀልም አኀዛዊ መረጃዎችም የወንጀለኞችን አሳብ የማስለወጥ አስተማማኝነት የለውም። ይህ ከሆነ ታዲያ መንፈስ ቅዱስ የሰውን መንፈስና ስሜት ነክቶ ለእውነተኛ ለውጥ ምክንያት መሆን ያስፈልገዋል ማለት ነው።

- ተሃድሶ ጮኾ መዘመርና መስበክ አይደለም።
- ተሃድሶ ቤተክርስቲያንን በሰው ለማጨናነቅ የሚደረግ ዘመቻ አይደለም። ቤተክርስቲያን በቁጥር ማደግዋ የተሃድሶ ውጤት ነው፤ ነገር ግን ቁጥር መብዛቱ ተሃድሶ አይደለም።
- ተሃድሶ የወንጌል ስርጭት አይደለም። ወንጌል ስርጭት የምስራቹን ማወጅ ነው። ተሃድሶ ወንጌል ስርጭትን ይቀድማል፤ ምክንያቱም መንፈሳዊነታቸው የሞተ አማኞች ላይ ተሃድሶ ሲመጣ ነው ወንጌሉን ተነስተው ሊያበስሩ የሚችሉት።
- ተሃድሶ ለየት ያሉ ዝግጅቶችን (Crusades, Meetings and Revivals) ማብዛት አይደለም። እውነተኛ ተሃድሶ ግን ለብዙ መንፈሳዊ ዝግጅቶች መደረግ ምክንያት ይሆናል።

## ታዲያ ተሃድሶ ምንድን ነው?

- ተሃድሶ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃል በተረዱና በሚታዘዙት ሰዎች ሕይወት በመጠቀም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድረውና ድንቅ ሥራውን የሚሠራው እግዚአብሔር ለትውልድ የሚያመጣው ትንሣኤ ነው።
- ተሃድሶ ከሰው አቅም ባለፈ ራሱን በራሱ ከሚያስተዳድረው ከእግዚአብሔር የሚሆን ነው፤ የእግዚአብሔር አድራጐት ነውና። ተሃድሶ እንዲመጣ በቃሉ ውስጥ የተገለጡትን መርሆዎች መከተል ግድ ይላል።
- ተሃድሶ መነቃቃት፣ መነሣሣት፣ መመለስ፣ እየደከመ ያለውን እንደገና ማበረታታት።
- ተሃድሶ ወደ ኀሊና ወይም ወደ ሕይወት መመለስ ነው። ትንሣኤ ያገኘው እንደገና ስለሚንቀሳቀስና ስለሚያፈራ ማለት ነው።
- ሊሞቱ ያሉትን ነገሮች እንደገና በመንፈሱ ማደስ።
- በጌታ ሕልውናው መታደስ ማለት ነው። "እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል" – የሐዋሪያት ሥራ 3፥19

## ለተሃድሶ መዘጋጀት

- ለተሃድሶ መዘጋጀትን ከግብርና ሙያ ጋር ልናስተያየው እንችላለን። አንድ ገበሬ መልካም አዝመራ ለማጨድ ቁጥ ብሎ ሊጸልይ ይችላል፤ ነገር ግን አስቀድሞ መሬቱን ካላዘጋጀ፣ ዘሩን ካልዘራና ውሃ ካላጠጣው ፍሬ መጠበቅ ሞኝነት ነው።
- በአንጻሩ መደረግ ያለበትን ሁሉ ስላደረግሁ ፍሬ ማግኘቴ እርግጠኛ ነው ብሎ የሚያስበውም ገበሬ ተላላ ነው። ምክንያቱም ዘሩ ለማፍራት የሚያስፈልገው ዝናብ፣ የጸሐይ ብርሃንና ትክክለኛው ካባቢ አየር በእግዚአብሔር የበላይነት ካልታገዘ ተገቢው ውጤት ሊገኝ አይችልም። አንድ ገበሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተደነገገው የመዝራትንና የማጨድን አምላካዊ ሕግ ተከትሎ ተግባሩን ቢያከናውንም፣ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ግን መቼውንም ቢሆን ያስፈልገዋል።

- ይህንኑ ምሳሌ ለተሃድሶ መጠቀም እንችላለን። ተሃድሶ ያለ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ለተሃድሶ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሰው ልብ መዘጋጀት ይኖርበታል። ተሃድሶ የእግዚአብሔር አድራጐትና የሰዎች ምላሽ ውጤት ነው።

## ተሃድሶ መቼ ነው አስፈላጊ የሚሆነው?

ተሃድሶ ሁልጊዜ ተፈላጊ ቢሆንም፣ አንድ ትውልድ ግን ወደኋላ ሲያፈገፍግ አስፈላጊነቱ የጎላ ይሆናል። ወደኋላ ስለማፈግፈግ ጉዳይ ኤርምያስ በምእራፍ 2፥19 ላይ እንዲህ ይላል፡- **"'ክፋትሽ ቅጣት ያስከትልብሻል፤ ክህደትሽም ተግሣጽ ያመጣብሻል፤ እግዚአብሔር አምላክሽን ስትተዪ፣ እኔንም መፍራት ችላ ስትይ፣ ምን ያህል ክፉና መራራ እንደሚሆንብሽ፣ አስቢ፤ እስቲ አስተውዪ፤' ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር።"** በተጨማሪም በምሳሌ 14፥14 ላይ **"ልባቸውን ከጽድቅ የሚመልሱ የእጃቸውን ሙሉ ዋጋ ይቀበላሉ"** ይላል።

ወደ ኤርምያስ ምእራፍ 2 እንመለስ። እስራኤል፡-

- እግዚአብሔር እንደቀድሞው አያስፈልገንም አለች። **"አባቶቻችሁ ከእኔ የራቁት፣ ከንቱ ነገርን የተከተሉት፣ ራሳቸውም ከንቱ የሆኑት፣ ምን ጥፋት አግኝተውብኝ ነው?"** – (ቁጥር 5)
- እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ታላላቅ ሥራዎች ረሱ። **"እነርሱም፣ 'ከግብፅ ምድር ያወጣን፣ በወና ምድረ በዳ፣ በጐድጓዳና በበረሐ መሬት፣ በደረቅና በጨለማ2፥6 ወይም *በሞት ጥላ* ቦታ፣ ሰው በማያልፍበትና በማይኖርበት ስፍራ፣ የመራን እግዚአብሔር ወዴት ነው?' ብለው አልጠየቁም። እኔ፣ ፍሬዋንና በረከቷን እንድትበሉ፣ ለም ወደ ሆነ መሬት አመጣኋችሁ፤ እናንተ ግን መጥታችሁ ምድሬን አረከሳችሁ፤ ርስቴንም ጸያፍ አደረጋችሁ።"** – (ቁጥር 6-7)
- ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ካሕናቱም "እግዝአብሔር ወዴት ነው?" አላሉም። **"'እግዚአብሔር ወዴት ነው?' ብለው፣ ካህናቱ አልጠየቁም፤ ከሕጉ ጋር የሚውሉት አላወቁኝም፤ መሪዎቹ ዐመፁብኝ፤ ነቢያቱም በበኣል ስም ተነበዩ፤ ከንቱ ነገሮችን ተከተሉ።"** – (ቁጥር 8)
- ፊታቸውን ከእግዚአብሔር ወደ አማልክት አዞሩ፤ እነርሱንም ለመፍትሄ ተስፋ አደረጉ። (ቁጥር 11-12፤ 27-28)
- **"ሕዝቤ ሁለት ኀጢአት ፈጽመዋል፣ ሕያው የውሃ ምንጭ የሆንሁትን፣ እኔን ትተዋል፤ ውሃ መያዝ የማይችሉትን ቀዳዳ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች፣ ለራሳቸው ቈፍረዋል።"** – (ቁጥር 13)
- በመንፈሳዊ ነገር እየዋለሉ ጠፉ። (ቁጥር 19)
- በራስ ጽድቅ ወደ መደገፍ መጡ። (ቁጥር 22-23)
- በከንቱ ሽፋን ራሳቸውን አጸደቁ። **"እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፤ "ከከሓዲዋ ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛዪቱ እስራኤል ጻድቅ ሆና ተገኘች።"** – (ኤርምያስ 3፥11) ከማታታለል ክሕደት ይሻል ነበር አለ ጌታ። ምክንያቱም ለመክዳት ድንጋጤ ይበቃል፤ ለማታለል ግን ሰው አስቦና አቀናብሮ የሚያደርገው ነው።
- በገቡበት ማጥ ሌሎችንም ይዘው ገቡ። (ቁጥር 33-34)

ማፈግፈግ በእኔነት እየተሞላን እግዚአብሔርን ከውስጣችን አሟጥጦ ማውጣት ነው። ልክ ውሻ ወደ ትፋቱ፣ እሪያም ወደ ጭቃ ረመጥ ጭቃው እንደሚመለስ ነው። (2ኛ ጴጥሮስ 2÷21-22)

## ከመንፈሳዊ ሕይወት የማፈግፈግ ምልክቶች

የሚከተሉትን ዝርዝሮች ስናነብ፣ ልባችንንና ሕይወታችንን በሚገባ እየመረመርን ይሁን። በአካሄዳችን እያፈገፈግን ነው የምንለው፦

1. የጸሎት ሕይወት አስፈላጊነት በእኛ ዘንድ እየመነመነ ሲመጣ። እንዲህ ዓይነት አባባል አለ፦ *"ተሃድሶ የሚዘገው ጸሎት ሲዘገይ ነው።"*
2. እስካሁን ባወቅነው ረክተን፣ ከዚህ በላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለመመርመርና ለመታዘዝ ጊዜ የመውሰዱ አስፈላጊነት አልታይ ሲለን። ልብ ልንል የሚገባን ነገር ቢኖር ይህ መጽሐፍ ቅዱስ አለማንበብን ሳይሆን በውስጡ ያሉት እውነቶች ከእውቀት አልፈው በሕይወታችን መተግበር ሲያቆሙ ማለት ነው።
3. ዘላለማዊ ለሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ያለን አትኩሮት ሲደበዝዝ፤ ማለትም በጊዜያዊው ነገር ብቻ ስንጠመድ።
4. በእውነተኛ ንስሃ ከመመለስ ይልቅ እግዚአብሔር ደካማ መሆኔን ያውቃል በማለት ኃጢአትን እንደ ቀላል ስናይ።
5. በሰዎች መሐል መንፈሳዊ ነገሮችን ለማውራት ስናፍር።
6. ከመንፈሳዊ ነገር ይልቅ መዝናናት፣ ስፖርት ወይም የመዝናኛ ጥበባት መድረኮች ቀዳሚ ሲሆኑ። (Entertainment, sports, arts, social media, internet)
7. ሕሊናችን ለኃጢአት ሲደነዝዝ።
8. ለቅድስና ያለን ሥፍራ በሕይወታችን እየቀዘቀዘ ሲመጣ።
9. አሳባችንን ቁስና ገንዘብ ማከማቸት አብዝቶ ሲወርስ።
10. የጌታ ስም ሲነቀፍ፣ በመንፈሳዊ ነገር ሲቀለድና ለዘላለማዊ ነገሮች ያለ ደንታ ቢስነት ስናይ በውስጣችን የሚነሣ ቅናትና እርምጃ ሲታጣ።
11. አምልኮ ድካም ሲሆንብን፣ ለቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ያለን ጉጉት ሲቀዘቅዝ፣ ከልብ ያልሆነ ዝማሬ ስንዘምር ወይም ከልባችን ዝማሬ ሲታጣ፣ በአምልኮ ውስጥ ያለውን ደስታ ስናጣው።
12. የቅዱሳን ሕብረት ሲታወክ አያገባኝም በሚል መንፈስ ስንመላለስ።
13. እጅግ ጥቃቅን ምክንያቶች ከቅዱሳን ሕብረት ሲያስቀሩን።
14. ራሳችንን መግዛት ሲያቅተን፤ ማለትም የማይገቡ ተንቀሳቃሽ የሆኑና ያልሆኑ ምስሎችን ስናይ፣ ለዘፈን ልባችን ሲከፈት፣ ግብረገባዊነት የሌላቸው ጽሑፎችንና ንግግሮችን ከማስተናገድ መቆጠብ ሲያቅተን።
15. በዕዳ የተያዘ ኑሮአችን፣ ውሸት፣ ያልታመነ ሕይወት፣ ቃላችንን ማጠፍ፣ አግባብ የሌለው አለባበስ፣ አሠሪዎቻችንን ማታለልና የመሳሰሉትን ነገሮች እንደ ተራ ነገሮች መቁጠር ስንጀምር።
16. ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለን ውስጣዊ ጥማት የሚያሳስበን ነገር መሆኑ እየቀረ ሲሄድ።
17. በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ዝቅተት እኔን አይመለከተኝም ስንል።

18. የዓለም ግብረገባዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መንፈሳዊና የኢኮኖሚ ሁኔታና ደረጃ እኔን አይመለከተኝም የሚል አስተሳሰብ እየወረሰን ሲሄድ።
19. ልባችን ሲደነድን፦ እንባ የሌለን፣ የማይገደን፣ ምላሽ ለመስጠት የማንነሣሣ ስንሆን። የእግዚአብሔርን እንባ የማንጋራ ሰዎች ስንሆን፤ እርሱ ግድ የሚለው ነገር እኛን ግድ ሳይለን ሲቀር።
20. መንፈሳዊ ጉልበት ከውስጣችን እንደጠፋ ሳናውቅ ስንቀር። ሳምሶም፦ “ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደተለየው አላወቀም ነበር።” (መሳፍንት 16÷20)

## ለተሃድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች

በብሉይ ኪዳን ለተሃድሶ ጸሎት የሚጠቅሙን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪዎች እናገኛለን። እያንዳንዱ ተሃድሶ ከሌላው ቢለይም ወደ ተሃድሶ መምጫው መንገድ ግን ተመሳሳይ ነው።

1. አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ተሃድሶዎች ከከፍተኛ መንፈሳዊ ዝቅተትና መከራ በኋላ የሚመጡ ናቸው። በዙሪያችን ያሉ ሁኔታዎች እየወረዱ ሲመጡ የተሃድሶ አፋፍ ላይ መድረሳችንን ያመለክታል!
2. እያንዳንዱ ተሃድሶ እግዚአብሔር ሌሎችን ለመቀስቀስ እጠቀምበታለሁ ብሎ ባሰበው በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ነው የሚጀምረው። እግዚአብሔር በተሃድሶ እሳት ልብህን ሲነካው፣ ሌሎች ይጐበኙ ዘንድ አንተም ይህንኑ እሳት ታራግባለህ።
3. እያንዳንዱ ተሃድሶ የሚያርፈው ኃይል ተላብሶ በሚታወጅ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው። የተሃድሶ መልእክት በኃጢአት፣ በገሃነም፣ በእግዚአብሔር ኃይል፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ መከናወን ላይ ሳይሆን በፍርድ ላይ ያተኮረ ነው። (ዘዳግም 11÷26-28፤ 1ኛ ሳሙኤል 7÷3፣ ሕዝቅኤል 33÷7-8፤ 1ኛ ነገሥት 18÷21)
4. ንሥሃ ሁልጊዜ ተሃድሶን ይቀድማል። ንሥሃ ጣኦታትን ማፍረስና ከዓለም መለየትን ይጨምራል።
5. ተሃድሶ እንዲመጣ መቅደም የሚገባው መቅደም አለበት። በቅዱሳን ሕብረት መትጋት፣ መስጠትና መሰጠት፣ የእግዚአብሐር ቃል፣ ወዘተ.
6. ወደ እውነተኛውና ንጹሕ አምልኮ መመለስ። ይህ አምልኮ ለብ ያለና ሥርዓት ለማከናወን ሲባል የተደረገ ሳይሆን ከፍጹም ልብና ነፍስ በደስታ የቀረበ ሊሆን ይገባል።
7. እያንዳንዱ ተሃድሶ በፍሬያማነት፣ በመከናወን፣ በታላድ ሐሴትና ደስታ የተሞላ ነው።

## የተሃድሶ እንቅፋቶች

በእግዚአብሔር የተሃድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚነሡ አንዳንድ እንቅፋቶችን ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት፦

### የመሪዎች እንቅፋትነት

በቤተክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማያስተምሩና የማይሰብኩ መሪዎች ተሃድሶን ያስተጓጉላሉ፤ ይህም የጸሎት ሕይወት፣ ቃሉን የመመርመር፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የመግለጥና ቃሉን ለመስበክ

የሚቃጠል ሕይወት የሌላቸው መሪዎችን ማለት ነው። ጉባዔውን በመጫን የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴ የሚገቱ መሪዎች የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ያደናቅፋሉ።

ለመንጋው የማይራሩ መሪዎች ለተሃድሶ ጠር ናቸው፤ ምክንያቱም መንጋው እንዲታደስ ወደ ለመለመ መስክና ውሃ አይመሩአቸውምና። ለሚጠፋው ዓለም የሚራራ ልብ ያጡ መሪዎች የተሃድሶ እንቅስቃሴ አደፍራሾች ናቸው። ብዙ መሪዎች በተሃድሶ ውስጥ ያላቸውን ዓይነተኛ ኃላፊነት አያስተውሉም። **"በጽዮን መለከትን ንፉ፤ ቅዱስ ጾምን ዐውጁ፤ የተቀደሰን ጉባኤ ጥሩ። ሕዝቡን ሰብስቡ፤ ጉባኤውን ቀድሱ፤ ሽማግሌዎችን በአንድነት አቅርቡ፤ ሕፃናትን ሰብስቡ፤ ጡት የሚጠቡትንም አታስቀሩ፤ ሙሽራው እልፍኙን ይተው፣ ሙሽሪትም የጫጉላ ቤቷን ትተው። በእግዚአብሔር ፊት የሚያገለግሉ ካህናት፣ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ አደባባይ መካከል ሆነው ያልቅሱ፤ እንዲህም ይበሉ፤ "እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕዝብህን አድን፤ ርስትህን በአሕዛብ መካከል መተረቻ፣ መሣቂያና መሣለቂያም አታድርግ፤ ለምንስ በሕዝቦች መካከል፣ 'አምላካቸው ወዴት ነው?' ይበሉን።" እነሆ፤ እግዚአብሔር ስለ ምድሩ ይቀናል፤ ስለ ሕዝቡም ይራራል።"** (ኢዮኤል 2፥15-18)

**የጉባዔ እንቅፋትነት**

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ጉባዔው ለተሃድሶ እንቅፋት ሆኖ ይገኛል። ጉባዔው ለወግና ለልማዶች ያለው ፍቅር ለተሃድሶ መሰናከል ሆኖ ይገኛል። ተሃድሶና ለውጥ የማይነጣጠሉ ባልንጀሮች ናቸው። እግዚአብሔር ልንተማመንበት የምንችለው የሥርዓት አምላክ ነው፤ ነገር ግን የአዲስ ነገር አምላክ ጭምርም ነው። እርሱ ባህል አጥባቂ አይደለም። ቤተክርስቲያን እንደሰዎች ባህል የምትመራ ከሆነ ከእግዚአብሔር መገኘትና ኃይል ውጪ መመላለስዋ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

አንድ ጉባዔ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ባለው ሥርዓት ፍቅር የተነደፈ ከሆነ ከፍተኛ የተሃድሶ እንቅፋት ነው። የንጉሥ ዳዊት የነበረችው ሜልኮል የንጉሡን ስሜታዊ አምልኮ ተቃውማ መካን ሆና ቀረች። ቤተክርስቲያንም ሰው ላወጣው ሥርዓትና የአምልኮ ዘይቤ ታላቅ ፍቅር ሲኖራት መካንነት ይጠናወታታል። ባዘጋጀነው የሁለት ሰዓት ስብሰባ ውስጥ እግዚአብሔር መጥቶ ተሃድሶን እንዲያደርግ ከመጠበቅ በላይ ምን ሞኝነት አለ? ተሃድሶ ከስብሰባ ያለፈ ጉዳይ ነውና።

ብዙ ጉባዔያት ከምቾት የማያስወጣ እውነት ይወዳሉ። ተሃድሶ ደግሞ በአንጻሩ ከምቾት የሚያስወጣ እውነት አለው። እግዚአብሔር በመንፈሱና በቃሉ በሚያመጣው እውነት ለመጠየቅ ራሳችንን ፈቃደኛ ማድረግ ይገባናል። ከዚህም በላይ በሌሎች ለመከበር ስንል ለተሃድሶ እንቅፋት እንሆናለን። አንዳንድ ጉባዔያት እግዚአብሔር ከሚለው ነገር ይልቅ ሰው የሚለው ግድ ይላቸዋል።

**ሌሎች እንቅፋቶች**

- በመሪዎችም ሆነ በጉባዔው ዘንድ በደል ሲገኝ የተሃድሶ እንቅፋት ይሆናል። **"እነሆ፤ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም መስማት አልተሳናትም ነገር ግን በደላችሁ ከአምላካችሁ ለይቶአችኋል፤ ኀጢአታችሁ ፊቱን**

**ከእናንተ ሰውሮታል፤ በዚህም ምክንያት አይሰማም።"** (ኢሳይያስ 59÷1-2) **"ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል።"** (ምሳሌ 28÷13)

- ይህ የመጨረሻው ዘመን ስለሆነ ነገሮች እየከፉና እየባሱ ነው የሚሄዱት የሚል መንፈስ ለተሃድሶ ትልቅ እንቅፋት ነው።
- ለጸሎትና ለቃሉ ያለ ቸልተኝነት፣ እንዲሁም ራስን አዋርዶ እግዚአብሔር የመፈለግ ልብ አለመኖር የተሃድሶ እንቅፋት ነው።
- የእግዚአብሔርን ልክ መወሰን ሊያመጣ ያለውን እንቅስቃሴ ይገድባል። **"ደግመው ደጋግመው እግዚአብሔርን ተፈታተኑት፤ የእስራኤልንም ቅዱስ አስቈጡት።"** (መዝሙር 78÷41) **"ባለማመናቸውም ምክንያት ብዙ ታምራትን በዚያ አላደረገም።"** (ማቴዎስ 13÷58)

## የእግዚአብሔር ተሃድሶ እቅድ

ከላይ የዘረዘርናቸው እንቅፋቶችን በምልጃ ጸሎት አማካኝነት ሊወገዱ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ተሃድሶ የጸሎት ምላሽ ስለሆነ። ለተሃድሶ በሚከተለው ጥቅስ መሠረት እንጸልይ፡-

> **"በስሜ የተጠራው ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ፣ ፊቴን ቢፈልግና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ እሰማዋለሁ፤ ኀጢአቱን ይቅር እላለሁ፤ ምድሩንም እፈውሳለሁ።"** (2ኛ ዜና 7÷14፤ አ.መ.ት.)

ብዙ የተሃድሶ ጸሎት መመሪያዎች በዚህ ጥቅስ ውስጥ ተካተዋል።

1ኛ/ **እግዚአብሔር የጠራው ሕዝቤ ...** በዚህ ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር የሚያናግራቸው ኃጢአተኞችን፣ ዓለምን ወይም ማንኛውንም ሰው ሳይሆን በስሙ የተጠራውን ሕዝብ ነው።

2ኛ/ ***ራሱን አዋርዶ ...*** ራስን ማዋረድ ማለት <u>በእግዚአብሔር ፊት ራስን ዝቅ ማድረግ</u> ማለት ነው።

> ***" 'ነገር ግን ለእኔ ያልታመኑበትንና በእኔም ላይ ያመፁበትን የራሳቸውን ኀጢአትና የአባቶቻቸውን ኀጢአት ቢናዘዙ፣ ይኸውም፣ እኔ ጠላት እንድሆንባቸውና ወደ ጠላቶቻቸው ምድር እንድሰዳቸው ያደረገኝን ኀጢአት ቢናዘዙ፣ ያልተገረዘው ልባቸው ቢዋረድና ስለ ኀጢአታቸው የሚገባውን ቅጣት ቢቀበሉ፣ በዚያ ጊዜ ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ኪዳኔን፣ ከይስሐቅም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን፣ ደግሞም ከአብርሃም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አስባለሁ፤ ምድሪቱንም አስባታለሁ።"*** (ዘሌዋውያን 26÷40-42)
>
> የኢዮስያስን ዘመን ተሃድሶ ስናጠና መዋረድ <u>በትህትና በእግዚአብሔር ፊት</u> (2ኛ ዜና 34÷1-13)፣ <u>በቃሉ ፊት</u> (2ኛ ዜና 34÷14-28)፣ እንዲሁም <u>በሕዝቡ ፊት</u> (2ኛ ዜና 34÷29-33) መቅረብ ማለት ነው።

3ኛ **ቢጸልይ ...** ጸሎታችን ቀጥተና ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔርን በመፈለግ ከክፉ መንገድ በመመለስ። አብዛኛውን ጊዜ ስለማንጠይቅ አንቀበለም። ግልጽና ቀጥተኛ የሆነ የንስሃ ጸሎት ለመጸለይ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ውስጣችንን እንዲያነቃቃ አስቀድመን እንጸልይ።

4ኛ ***ፊቴን ቢፈልግ ...*** የእግዚአብሔርን ፊት ስለመፈለግ ጉዳይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጥቅሶች እናነባለን።

(ዘጸዓት 33÷7፤ ዘዳግም 4÷29፤ ዕዝራ 8÷22፤ 2ኛ ሳሙኤል 12÷16፤ 21÷1፤ 1ኛ ዜና 16÷10-11፤ 2ኛ ዜና 7÷14፤ 11÷16፤ 15÷4፤ 20÷4፤ መዝሙር 105÷3-4፤ 24÷6፤ 27÷8፤ 40÷17፤ 69÷7፤ 70÷5፤ ምሳሌ 28÷5፤ ኢሳይያስ 51÷1፤ ኤርምያስ 29÷13፤ 50÷4፤ ሆሴዕ 3÷5፤ 5÷6-7፣ 15፤ 7÷10፤ ዳንኤል 9÷3፤ ሰፎንያስ 1÷6፤ ዘካሪያስ 8÷21፤ ሚልክያስ 3÷1)

በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት እግዚአብሔርን መፈለግ የሚከተሉትን ነገሮች ይጠይቃል፦

- በገዛ ፈቃዳችንና በሙሉ ልባችን ወደ እግዚአብሔር ፊታችንን መመለስ ይጠይቃል።
- እርሱን ለማገልገል ውስጣዊ የመሰጠት መንፈስ ይጠይቃል።
- ከክፉ መንገዳችን መመለስን ይጠይቃል።
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ውሳኔ ይጠይቃል።
- ለልባዊ ጸሎት ያለ ዝግጁነትን ይጠይቃል።

እግዚአብሔርን መፈለግ ከክፉ ለመሸሽ ቀዳሚ እርምጃ ነው። **"እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት እንዲህ ይላል፤ 'እኔን ፈልጉ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ።' … በሕይወት ትኖሩ ዘንድ፣ መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ"** (አሞጽ 5÷4፣ 14) እግዚአብሔርን መፈለግ ለህለወቱ ወሳኝ ነው። **"በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ፣ ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤ ፊቴን ይሻሉ፤ በመከራቸውም አጥብቀው ይፈልጉኛል።"** (ሆሰዕ 5÷15)

**5ኛ ከክፉ መንገዱ ቢመለስ …**

ጸሎትና እግዚአብሔርን መፈለግ እጅግ በጣም አስፈላጊ እርምጃዎች ቢሆኑም፣ ተሃድሶ የሚመጣው እውነተኛ ንስሃ ሲታከልባቸው ነው። ከክፉ መንገዳችን ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ጉዳይ የግድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፉልን የተሃድሶ እንቅሳቃሴዎች ሁሉ ንስሃ የጎላ ድርሻ አለው። ቤተክርስቲያን በሐዋሪያት ሥራ ምእራፍ 2 ጀምራ እስከ የዩሐንስ ራእይ ምእራፍ 22÷16 ድረስ የንስሃ ጥሪ ታደርጋለች።

ንስሃ የሕይወታችንን አቅጣጫ ለመቀየር የሚያስችለን የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው። (የሐዋሪያት ሥራ 5÷29-31፤ 11÷15-18፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2÷22-26)። ሰው ሁሉ ንስሃ እንዲገባ ታዝዞአል (የሐዋሪያት ሥራ 17÷30)። ንስሃም እንድንገባ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 3÷9)፤ እንዲሁም እግዚአብሔር በጸጋው ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ ይጠራቸዋል (ሮሜ 2÷4)። ንስሃ የማይገባ ይጠፋል (ሉቃስ 1÷3፣ 5)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ንስሃና የኃጢአት ስርየት ለአሕዛብ ሁሉ በስሙ እንዲሰበክ አዝዞአል (ሉቃስ 24÷47)።

እያወቅን ስላላደረግነው መልካም ነገር፣ ሆን ብለን ስላደረግነው ኃጢአት፣ የእርሱን ምክር ባለመፈለግ ስለሄድንባቸው መንገዶች ሁሉ ንስሃ ልንገባ ያስፈልጋል። በተጨማሪ ንስሃ ከሞተ ሥራ ፊታችንን የምንመልስበት መንገድ ነው ። **"ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባትና6፥1 ወይም *ከከንቱ ሥርዐት* በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ ገና መሠረትን አንጣል …"** (ዕብራውያን 6÷1)።

ከንጹሕ አምልኮ (በመንፈስና በእውነት ማምለክ)፣ ከአሥራትና ስጦታ፣ በቸርነት ለሌሎች ከመትረፍ በጎደልንበት ሁሉ ንሥሃ ልንገባ ያስፈልጋል።

**"ከሞተ ሥራ"** ሲል ካለመንፈስ ቅዱስ የምናቀርበው አገልግሎት ሁሉ የሞተ ሥራ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜ መንፈሳዊ ሕይወታችንን፣ የልባችንን ምኞትና አገልግሎታችንን ልንመዝን ይገባል።

## ማጠቃለያ

ለተሃድሶ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን በሙሉ ልብህ አድርጋቸው፡-

- ራስህን አዋርድ (በትህትና በእግዚአብሔር ፊት ቅረብ)
- ጸልይ
- የእግዚአብሔርን ፊት ፈልግ
- ከክፉ መንገድህ ተመለስ

የሚከተሉት ደግሞ የእግዚአብሔር ምላሽ ናቸው፡-

- እግዚአብሔር ከሰማይ ይሰማሃል - ይመልሳል።
- ይቅር ይልሃል - ያስታርቅሃል።
- ምድርህን ይፈውሳል - ያድስሃል።

# ማስታወሻ

# ክፍል 8
# ምልጃን መጀመርና ማቀጣጠል

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች እንማራለን፡-

- ለተቀናበረ ጸሎት እቅድ ማውጣት
- ለግል ጸሎታችን መመሪያን ማዘጋጀት
- ምልጃን በመጀመርና በማቀጣጠል ውስጥ የሚነሡትን ችግሮች ማጥናትና መፍትሄዎችን ማዘጋጀት
- ምልጃን ማድረግ አለብኝ ከሚል መንፈስ ወደ ደስታ ማሻገር
- ለምልጃ አገልግሎት መስጠት

### ቁልፍ ጥቅስ፡-

> **"አንተ ግን ስትጸልይ ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል።"** (ማቴዎስ 6፥6፤ አ.መ.ት.)

### መግቢያ

የምልጃን አገልግሎት ማጥናት ከጀመርን፡-

- ምልጃ ምን እንደሆነ
- ለምልጃ የሚያስፈልጉንን መንፈሳዊ ምንጮች
- የምልጃን ጸሎት እንዴት እንደምንጸልይ
- ለምልጃ ምሳሌ የሚሆነን የጌታ ኢየሱስን ሕይወት
- እንዲሁም የምልጃን እንቅፋቶች ተመልክተናል።

ይህ የመጨረሻው ክፍል ምልጃን ከግል ሕይወታችን አንሥተን እስከ ምልጃ አገልግሎት ልናሳድግ የምንችልባቸውን መንገዶች ይጠቁመናል።

## ለተቀናበረ ጸሎት እቅድ ማውጣት (ቅርጽ ያለው ጸሎት)

ፍሬያማ የምልጃ አገልግሎት ከፈለግን ለጸሎት ጊዜ መመደብ ይኖርብናል። ይህንን ተግባራዊ የምናደርግበት አንዱ መንገድ አስቀድሞ ዕለታዊና ቋሚ የግል ጸሎት ጊዜ መመደብና ከሌሎች ጋር በሕብረት የምንጸልይበት ጊዜ ማቀድ ነው። አዲስ ኪዳን የጸሎት ተዋጊዎችን ለማስነሳትና ለማነሳሳት የሚከተለውን አሠራር ያመለክተናል።

## የግል ጸሎት

ጸሎት በግልና በስውር ሊደረግ ይገባል።

> **"አንተ ግን ስትጸልይ ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል።"** (ማቴዎስ 6÷6፤ አ.መ.ት.)

በየዕለቱ ለጸሎት የተለየ ጊዜ መድብ፤ በተለየም በማለዳ ከሁሉ አስቀድሞ ቢሆን ይመረጣል። የጠዋት ሰው ካልሆንክ ሌላ የሚመችህን ጊዜ መምረጥ ትችላለህ። ይህ በግል ጥሞና በእግዚአብሔር ፊት በምስጋናና በአምልኮ ቆመህ የክሕነት ተግባርህ የምትፈጽምበት፤ እንዲሁም በሰውና በእግዚአብሔር መሐል ቆመህ የምትጸልይበትና የምትማልድበት ጊዜ ነው። ከምልጃ በማስቀደም ንስሃ ልትገባ በሚያስፈልግህ ነገር ሁሉ ንስሃ ግባ፤ ይህ ለፍሬያማ ምልጃ ወሳኝ ነውና።

## ሁለት ሆኖ መጸለይ

ሁለት ሆኖ መጸለይ የሕብረት ጸሎት ትንሹ ቁጥር ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንና በሚከተለው ጥቅስ በውስጡ ያለው ኃይል የሚገለጥበት ጸሎት ነው።

> **"ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለ ምንም ነገር በመስማማት ብትጠይቁ በሰማይ ያለው አባቴ ያደርግላችኋል"** – ማቴዎስ 18÷19

አንድ የምልጃ ጸሎት አገልጋይ መሆን የሚፈልግ አጋር ፈልግና በቋሚነት አብረኸው ጸልይ። ባለትዳር ከሆንክ የትዳር ጓደኛህን ለዚህ ዓላማ ልትመርጥ ትችላለህ። አብረን የምንጸልየው ሰው ካለ በምንደክምበት ጊዜ ሊያበረታታንና እኛም በተራችን ልናበረታታው እንችላለን።

## **አነስተኛ ሕብረቶች** (Cell groups, Bible Study groups, small groups)

አነስተኛ ስንል ከሁለት በላይ አማኞች ለምልጃ አገልግሎት የሚሰበሰቡባቸውን ሕብረቶች ነው። ለምልጃ አገልግሎት ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ሲሰበሰቡ ታላቅ ኃይል አለው።

> **"ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁና።"** – ማቴዎስ 18÷20

በየሳምንቱ በአነስተኛ ሕብረቶች ውስጥ፣ አማኝ ከሆኑ የሥራ ባልደረቦቻችን ጋር፣ ወይም ዘመዶቻችን ጋር ለምልጃ ጸሎት መገናኘት እንችላለን።

## የጉባዔ ጸሎት

ለምልጃ በቤተክርስቲያን ደረጃ በአንድነት ተሰባስቦ መጸለይ ተገቢ ነው።

> **"ጴጥሮስም በዚህ መሠረት እስር ቤት ተጣለ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ስለ እርሱ አጥብቃ ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ ነበር።"** – *የሐዋሪያት ሥራ* 12÷5

ጴጥሮስ በእስር ቤት በተጣለ ጊዜና ሄሮድስ እርሱንም እንደ ዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ለማስገደል አስቦ ባሳሠረው ጊዜ፣ በቤተክርስቲያን የምልጃ ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። በቤተክርስቲያን እንዲህ ያለው ጸሎት በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ሊካሄድ ይገባል።

## ለግል ጸሎታችን መመሪያን ማዘጋጀት

ምልጃችን ቀጥተኛ እንዲሆን የጸሎት መመሪያ ማውጣት አላማችንን በእጅጉ ያግዘዋል። ለዚህም መከፋፈያ ያለው የግል ደብተር ቢሆን ይመረጣል፤ ይህም ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱትን ዝርዝር የጸሎት አቅጣጫዎችና ማስታወሻዎች በየገዛ ክፍልፋያቸው ለመጻፍ ስለሚያስችለን ነው። እያንዳንዱ ክፍልፋይ የሚከተሉትን እንዲይዝ አድርገን ማዘጋጀት እንችላለን፡-

- <u>ጥናት</u>፡- ስለምልጃና ጾም የምናደርጋቸውን ጥናቶች የምንጽፍበት
- <u>ሃገር አቀፍ ጸሎት</u>፡- የከተማችንን፣ የምንኖርበትን አገረ ግዛትና የምንኖርበትን አገር ካርታ፣ እንዲሁም የመንግሥት ባለሥልጣናትንና የቤተክርስቲያን መሪዎችን ስም መዝግበን በስማቸው ለመጸለይ የሚያስችለንን መረጃ የምናስቀምጥበት
- <u>ለግል የምልጃ ጸሎት</u>፡- ለቤተሰባችን፣ ለወዳጆቻችንና ለሌሎች በየእለቱ የምንጸልይባቸውን ርእሶችንና ያበረታታን ዘንድ የተመለሱትን ጸሎቶች የምንመዘግብበት
- <u>ስለ ቤተክርስቲያናችን</u>፡- በየእለቱ እንጸልይ ዘንድ በቤተክርስቲያናችን ያሉትን የመሪዎችንና የአገልጋዮችን ስም ዝርዝርና የተገለጡ የጸሎት ርእሶች የምንጽፍበት
- <u>ስለ አገልግሎታችን</u>፡- ለግል አገልግሎታችን ልንጸልይ ይገባል። የምናገለግላቸው ሰዎች ካሉ ለእያንዳንዳቸው እንድንጸልይ ስማቸውን የምንመዘግብበት፣ ወላጅ ከሆንን ለልጆቻችን የምንጸልይበትን የጸሎት ርእስ የምንመዘግብበት፣ ወዘተ …
- <u>ዓለም አቀፍ ጸሎት</u>፡- የምንጸልይላቸውን አገሮች ስም ዝርዝርና የጸሎት ሸክም በተለይም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት ጉዳይ የምንጽፍበት

## ምልጃን በመጀመርና በማቀጣጠል ውስጥ የሚነሡትን ችግሮች ማጥናትና መፍትሄዎችን ማዘጋጀት

እያንዳንዱ የጸሎት ሰው በየጊዜው ሊያሸንፋቸው የሚገባው እክሎች በሕይወቱ ይጋፈጣል። እነዚህን ተግዳሮቶች ድል መንሣት የምልጃ አንዱ ክፍል ነው።

> *"በጸሎት መትጋት ማለት በጸና የጸሎት ሕይወት እንዳንቀጥል ተገዳዳሪ በሆኑ እንቅፋቶች ውስጥ በቁርጠኝነት ተዋግቶ ማለፍ ነው። ይህ ማለት ደግሞ በጸሎት ሕይወታችን ደክመን ላለመገኘት አሊያም ከደከምንም በመንፈስ ቅዱስ እየታደስን ዘወትር ነቅተን መጠበቅ ነው።"* — ዶ/ር ኦ. ሆልዝቢ

እያንዳንዱን ተግዳሮት በጸሎት መንፈስ ሊያድሰን በሚችለው በእግዚአብሔር ፊት እናምጣው። እስቲ በጸሎት ሕይወት የሚገጥሙንን የተለመዱ ችግሮች እንመልከት፡-

### ጊዜ ማጣት

የሰው ልጆች ስንባል ከልብ ለምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ጊዜ አለን። ጊዜ የለኝም ማለት በቂ ምክንያት አይሆንም። ሥራ በበዛበን ቁጥር አብዝተን ልንማልድ ያስፈልገናል። ይልቁን ለጸሎት ጊዜ እንመድብና ያንን ጊዜ በምንም ዓይነት መንገድ ላለማስነካት እንወስን። ለጸሎት የምንመድበው የጊዜ መጠን ከማንም የጸሎት ጊዜ መጠን ጋር በማስተያየት ሳይሆን፣ በውስጣችን ያለውን ሸክም ለማፍሰስ ከሚያስፈልገን ጊዜ ጋር አስተያይተን እንመድብ። ምልጃ ስላስረዘምነው ፍሬያማ ይሆናል ማለት አይደለም። እስቲ በክርስቶስ ቀኝ ተሰቅሎ የነበረውን ወንበዴ ጸሎት ፍሬያማነት እናስብ? ወይም ደግሞ የዚያን የቀራጩን ልባዊና አጭር ጸሎት ከረጅሙና ከራስ ጽድቅ ከመነጨው ከፈሪሳዊው ጸሎት ጋር እናስተያየው?

### የሃሳብ መከፋፈል

በምልጃ ጸሎት ወቅት የተለያዩ መስተጓጉሎችን እናስወግድ። በጸሎት ጊዜያችን እንዳትረበሽ ስልኮችን አንቀበል ወይም እናጥፋ፣ በምንጸልየበት አካባቢ ላሉ ቤተሰቦች፣ ባልደረቦች፣ ወይም ወዳጆች መረበሽ እንደማንፈልግ እንግለጥላቸው፣ ማንኛውን አሳባችንን ሊሰርቅ የሚችል ነገር ከእኛ እናርቅ። አንዳንድ ጊዜ የመዝሙር ቅጂዎችን ማጫወት በአካባቢያችን ያሉትን ሌሎች ድምጾችን ሊያደበዝዝልን ይችላል።

### የሰውነት ድካም

በጸሎት ጊዜ ይደክመኛል ብለህ የምታስብ ከሆነ ከመጸለይህ በፊት ሰውነትህን በተለያዩ መንግዶች ማነቃቃት ትችላለህ። ገላን ወይም ፊትን መታጠብ፣ ከሙብላትህ በፊት መጸለይ ወይም ከጸሎት በፊት ከበድ ያሉ ምግቦችን አለመመገብ፣ በተቻለ

አቅም የምንጸልይበትን ቦታ አየር ተስማሚ ማድረግ፣ በምንጸልይበት ጊዜ ከመንበርከክ ይልቅ ቆሞ ወይም እየተመላለሱ መጸለይ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን መጠቀም ይቻላል።

## ለመጸለይ ፍላጎት ማጣት

ለእንዲህ ዐይነቱ ችግር ለምልጃ ጸሎት ያለን ፍላጎት እያደገ የሚሄድበትን መንገድ መቀየስ እንችላለን። ይህም የሚጀምረው ቢሰማንም ባይሰማንም ወደ ጸሎት በመሄድ ነው። ምክንያቱም ክርስትና በአጠቃላይ በእምነት ላይ እንጂ በስሜት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ስለ ራሳችንና ስለ ሌሎች የምናቀርበውን ምልጃ ውጤት በየዕለቱ እያየን ስንመጣ፣ ያ ራሱ የጸሎት ሕይወታችንን እያቀጣጠለ *"ማድረግ አለብኝ"* ከሚለው መንፈስ መሆኑ ይቀርና በደስታ የምናከናውነው ይሆናል።

## ለምልጃ አገልግሎት መሰጠት

> **"የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ምሎአል፤ 'እንደ ፀቀድሁት በርግጥ ይከናወናል፤ እንደ አሰብሁትም ይሆናል።'"** – ኢሳይያስ 14÷24

በምልጃ ሕይወት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ ሕይወት ታደርጋለህ። የእግዚአብሔርንም ልብ ተረድተህ ትጸልያለህ።

> **"ለምድር ሁሉ የታሰበው ዕቅድ ይህ ነው፤ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋው እጅ ይኸው ነው። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አስቦአል፤ ማንስ ያግደዋል? እጁም ተዘርግቶአል? ማንስ ይመልሰዋል?"** – ኢሳይያስ 14÷26-27

እግዚአብሔር የዘላለም አሳብ አለው፤ ይህንን አሳቡን የዓለም ይሁን የሥጋ፣ የኢጋንንት ይሁን የገሃነም፣ ራሱ ሰይጣንም ሊያስቆመው አይችልም። እኛም በዚህ የምልጃ ጸሎት አገልግሎት የዘላለማዊ አሳቡ ተካፋዮች ሆነናል።

| ለዚህ የምልጃ አገልግሎት ራሳችንን በሙላት ዛሬ እንስጥ! |
|---|